# የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
# የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል


## ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ ፍተሻ (አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኩዋሪነት)


በ

ተሰፋነሽ አምባዬ


ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


ጥር፣ 2015ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ፤ኢትዮጵያ

# ጅማ ዩኒቨርሲቲ
# የድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት
# የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል

## ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ ፍተሻ (አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኩዋሪነት)


በ

ተሰፋነሽ አምባዬ


ለአማርኛ ማስተማር ማስተርስ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት


አማካሪ፡ ማንያለው አባተ(ዶ/ር)



ጥር፣ 2015ዓ.ም

ጅማ ዩኒቨርሲቲ፤ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሰቲ

የሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲ ኮሌጅ

የኢትዮድያ ቋንቋ (ዎች)ና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

በማህበራዊ ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋ (ዎች) እና ስነ-ፅሁፍ ( አማርኛ) ክፍለ ትምህርት

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

**ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ ፍተሻ (አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ የቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኩዋሪነት)** በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት በተስፋነሽ

**አምባዬ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱአ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡**

የፈተና ቦርድ አባላት፤

ዋና አማካሪ ..........................................ፊርማ.............................ቀን..................

ረዳት አማካሪ....................................ፊርማ..........................ቀን.................

የውጭ ፈታኝ .............................................ፊርማ.........................ቀን.......................

የውስጥ ፈታኝ .............................................ፊርማ.........................ቀን........................

## የአማካሪዎች ይሁንታ

ተማሪ ተስፋነሽ አምባዬ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ተማሪ ስትሆን የመመረቂያ ጥናቱዋን ከአማካሪዎቹዋ ጋር በትብብር እየሰራች የቆየች ስለሆነ ለተቋቁሞ መቅረብ የምትችል መሆኑን እናረጋግጣለን፡፡

ዋና አማካሪ ስም፡- -------------------- ፊርማ ------------------- ቀን ----------------

ረዳት አማካሪ ስም ፡- ------------------ ፊርማ-------------------- ቀን-----------------

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ ከብዙ ነገር ጠብቆ ፍቃዱ ሆኖ ለዚህ ላበቃኝ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፡፡ በመቀጠል ከርዕስ መረጣ ጀምሮ ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ በረቂቁ እርማትም ሆነ በማስተካከያ አሰጣጥ ጠቃሚ ምክሮችንና ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት የዳበረ ሙያዊ ድጋፋቸው ያልተለየኝ አማካሪዎቼን ማንያለው አባተ(ዶ/ር) እና ጥበበ ሽቴ (ዶ/ር) ከልቤ አመስግናለሁ፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ጥናቱ በተካሄደበት ቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት ላገዙኝ የት/ት ቤቱ ር/መምህር እና መምህራን እንዲሁም መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ተማሪዎች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ የአፋን ኦሮሞ አፊ-ፊት ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ መፈተሸ ነው፡፡ ጥናቱ የተካሄደው በጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ ቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ት ቤት በ2015ዓ.ም በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ የተሰበሰበው መረጃም ከጥናቱ ዓላማና መሪ ጥያቄዎች አንጻር በገላጭ ስታቲስቲክስ በመታገዝ ተብራርቷዋል፡፡ በመረጃው ትንተና መሠረት በተማሪዎቹ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነት ጥሩ ደረጃ የታየ ሲሆን ነገር ግን የአማርኛ ፈተና ውጤታቸው ከተነሳሽነታቸው ጋር ሲነጻጸር ዝቅተኛ ሆኖ ታይቷዋል፡፡ ከጥናቱ ውጤትም በመነሳት አጥኚዋ የሚከተሉትን የአስተያየት ነጥቦች አስቀምጣለች፡፡ በክፍል ውስጥ የቋንቋ መምህራን የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት መኖር ወይም አለመኖር በትምህርት ውጤታቸው ላይ የበኩሉን ተጽእኖ እንደሚያሳድር በመገንዘብ፣ የቋንቋ ትምህርቱን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ ቢያቀርቡ፤ መምህራን ከትምህርት አቀራረባቸውም በተጨማሪ የተማሪውን ተነሳሽነት ወደ ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ ስልቶችን በመጠቀም የተማሪዎች የውጤት መሻሻል ላይ ቢሰሩ፤ የሰርዓተ ትምህርት ቀራጮችና የትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች በዝግጅታቸው ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን የተነሳሽነት ሁኔታ ከግምት ቢያስገቡ፤ በአጠቃላይ ኢ-አፊፊት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነታቸው የጎላ ሊሆን የሚችል ቢሆንም በውጤት ረገድ ዝቅተኛ ሊሆኑ ስለሚችሉ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚሉት በአጥኚዋ የተቀመጡ የመፍትሄ ሀሳቦች ናቸው፡፡

ማውጫ


ምስጋና ..... i

አጠቃሎ ..... ii

የሰንጠረዥ ማውጫ ..... v

ምእራፍ አንድ፡ መግቢያ ..... 1

1.1 **የጥናቱ ዳራ** ..... 1

1.2 **የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት** ..... 5

1.3 **የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች** ..... 6

2. የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ..... 6

1.4. **የጥናቱ ዓላማ** ..... 7

1.4.1 የጥናቱ ዋና አላማ ..... 7

1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ..... 7

1.5 **የጥናቱ ጠቀሜታ** ..... 7

1.6. **የጥናቱ ወሰን** ..... 8

1.7. **የቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ** ..... 8

ምዕራፍ ሁለት ..... 10

ክለሳ ድርሳናት ..... 10

2.1. **ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት** ..... 10

**2.1.1 የተነሳሽነት ጽንሰ-ሀሳብ ታሪካዊ አመጣጥ** ..... 10

**2.1.2 የተነሳሽነት ምንነት** ..... 12

**2.1.3 የተነሳሽነት አስፈላጊነት** ..... 13

2.1.4 የተነሳሽነት መገለጫዎች (ገጽታዎች) ..... 16

**2.1.4.1 ግለ ብቃት (Self Eficacy)** ..... 16

**2.1.4.2 ግለ መር (Self Regulation)** ..... 17

**2.1.4.3 ግለ ግንዛቤ (Self Concept)** ..... 18

**2.1.5 የተነሳሽነት አይነቶች** ..... 19

**2.1.6 ተነሳሽነትና የወደፊት ግብ ተዛምዶ** ..... 21

**2.1.7 የተነሳሽነት መኖር አለመኖሩ የሚታወቅባቸው መንገዶች** ..... 22

**2.1.8 በተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች** ..... 26

**2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት** ............ 32
ምዕራፍ ሶስት ............ 43
የጥናቱ ንድፍና አካሄድ ............ 43
**3.1. የጥናቱ ንድፍ** ............ 43
3.2 የናሙና አመራረጥ ............ 43
**3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች** ............ 44
**3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ** ............ 45
ምዕራፍ አራት ............ 48
የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ ............ 48
4.1 የመረጃ ትንተና ............ 48
**4.2. የውጤት ማብራሪያ** ............ 51
ምዕራፍ አምስት ............ 54
ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ ............ 54
**5.1. ማጠቃለያ** ............ 54
**5.2. መደምደሚያ** ............ 55
**5.3. የመፍትሄ ሀሳብ** ............ 55
ዋቢ መጻህፍት ............ 57

## የሰንጠረዥ ማውጫ


*ሠንጠረዥ 1፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃና የፈተና ውጤት……………………..……50*

ሠንጠረዥ 2 ተማሪዎች ለት/ት ያላቸው ተነሳሽነት አጠቃላይ ደረጃ……………..………….51

*ሰንጠረዥ 3፡ የተነሳሽነት አቅጣጫዎች እና የአማርኛ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ………….52*

# ምእራፍ አንድ፡ መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ተነሳሽነት ሰዎች አንድን ተግባር እንዲፈጽሙ የሚገፋፋ ውስጣዊ ስሜት ነው Harmer (1991)፡፡ ይህንኑ ፅንሰ ሀሳብ Brown (1987) ተነሳሽነት በሰው ልጆች ላይ የሚታይ ተፈጥሯዊ የሆነ አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ውስጣዊ ፍላጎት መሆኑን ያብራራሉ፡፡ይህም የሚያሳየን ተነሳሽነት የተለያዩ ዓላማዎችን መሰረት በማድረግ አንድ ነገር ለምንና እንዴት እንደሚተገበር የሚያሳይ የባህሪይ ተፅዕኖ ሊያመጣ የሚችል ግፊት መሆኑን ነው፡፡

ከቋንቋ ትምህርት ምርምር ትኩረቶች መካከል አንደኛው የተማሪዎች ተነሳሽነት ነው (Rubinson 2001 እና Harmer 1991)፡፡ ተነሳሽነት የማንኛውም ውስብስብ ተግባር ስኬታማነት ወይም ስኬት አልባነት መገለጫ ነው (Brown 1994)፡፡ የአእምሮና የስሜት መቀስቀስ ሁኔታ፣ አንድን ነገር ለመተግበር ወደውሳኔ የሚመራ፣ ዘላቂነት ወዳለው አእምሯዊና አካላዊ ጥረት የሚያነሳሳ፣ ቀድሞ የታቀደ ግብን ለማሳካት የሚረዳ፤ በሚልም ይገለፃል (William ና Burden 1997)፡፡ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አንፃርም እንደትምህርት ውጤት መገለጫ ሆኖም ያገለግላል፤ ከዚህም በተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከቋንቋ መማር ሂደት ጋርም ግልፅ የሆነ ግንኙነት አለው (Gardner 1985)፡፡ በጎ ምኞትና ጥረት የተነሳሽነት አንድ መከሰቻ ቢሆኑም ብቻቸውን ግን የተነሳሽነትን መኖር አያመለክቱም (Gardner, 1985)፡፡ መነሳሳት ያላቸው ሰዎች ዓላማቸውን ለማሳካት ጥረት ሊያሳዩ ይችላሉ፤ ጥረት የሚያሳዩ ሰዎች ሁሉ ግን ተነሳሽነት አላቸው ማለት አይደለም፡፡ በቋንቋ ትምህርት ለምሳሌ የተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች (መምህርን ወይም ወላጅን የማስደሰት ምኞትና ከፍተኛ ውጤት የማስመዝገብ ፍላጎት) ተማሪዎች ጥረት እንዲያደርጉ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ግለሰብ ቋንቋውን ለመማር ሊፈልግ ይችላል፤ ከዚህም ጋር በተያያዘ በሚያደርጋቸው ተግባራት ሊደሰት ይችል ይሆናል፤ ፍላጎቱና የደስታ ስሜቱ ጥልቅ በሆነ ጥረት ካልተደገፉ ግን ተነሳሽነቱን በትክክል አያመላክቱም፡፡ ስለዚህም ዓላማን የማሳካት ምኞትና ለዓላማው የሚኖሩት በጎ አመለካከቶች ከጥረት ጋር ሲገናኙ ብቻ ነው ተነሳሽነት አለ ማለት የሚቻለው፡፡

ተነሳሽነትን ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከተው እንደ ትምህርት ውጤት መግለጫ ሆኖም ያገለግላል Gardner (1985)፡፡ አክለውም ጋርድነር ከዚህም በተጨማሪ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከቋንቋ መማር ሂደት ጋርም ግልጽ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እንደ ጋርድነር አገላለጽ ተነሳሽነት የጥረት ቋንቋ የመማር ዓላማን የማሳካት፣ ምኞትና ቋንቋ ለመማር የሚያስችሉ የጥሩ አመለካከቶች ቅንጅት ነው፡፡ ይህም የሰዎችን ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት የሚያንፀባርቅ ከውስጣዊ ወይም ከውጫዊ ግፊት በመነሳት ቀና አመለካከትን፣አዎንታዊ ምላሽን እና ጥሩ ውጤትን የሚያስገኝ አንድ ድርጊት እንዲፈፀም የሚያበረታታ ሂደት መሆኑን ያመለከታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ግለሰቡ ቋንቋውን ለመማር ካለው ምኞትና ከተግባር ለሚያገኘው እርካታ ሲል የሚያከናዉ ነው ስራ ወይም የሚያደርገው ጥረት እንደሆነ ይስተዋላል፡፡

Brown, (2000). ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ውህዳዊና ጥቅማ ጥቅማዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል፡፡ ውህዳዊ ተነሳሽነት የሚባለው የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት ጋር ውህደት ወይም ቅርበት ለመፍጠር ከማሰብ አኳያ ቋንቋውን ለመማር የሚነሳሱበት የተነሳሽነት ዓይነት ነው Ellis, (1995)፡፡ ይህም ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋና ባህል፣ማህበራዊ አኗኗር፣ መልካም አመላካከት ስለሚኖራቸው ቋንቋውን ለመማር የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጠንካራ ሊሆን እንደሚችል ያስረዳል፡፡

ሌላው የተነሳሽነት ዓይነት ከውህዳዊ ተነሳሽነት ጋር አብሮ የሚነሳው ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ተጨባጭ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ቋንቋውን የሚማሩበት የተነሳሽነት ዓይነት ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ይባላል Ellis ,(1997)፡፡ ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን Norris, (2001). አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ የሚማሩበት ዓላማ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርት ለማሟላት የተሻለ ደመወዝ ወይም ክፍያ ለማግኘት ዓለምአቀፋዊ መረጃና ዕውቀት ለማግኘት የሚሉት ዋና ዋና የጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት ዓላማዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

ሌሎች በምሁራን ተደጋግመው የሚነሱት የቋንቋ መማር የተነሳሽነት ዓይነቶች ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳሽነት የሚባሉት ናቸው Brown.H.D. (2000)፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ከውስጥ በሚመነጭ ግፊት በመማር ተግባራትን በማከናወን የሚገኝ የተነሰሽነት ዓይነት ሲሆን ተመሪዎቹ የመምህሩ የማስተማር ስልት ቢያረካቸውም ባያረካቸውም ትምህርቱ ፈተና ይኑረው አይኑረው ቋንቋውን ከመማር ወደ ኋላ የማይሉበት የተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡ የውስጣዊ መነሳሳት ባህሪያት ውስጣዊ ምላሽ የሚያስገኙ ውጤቶች ሲሆኑ እነዚህም የብቃት ስሜቶችና ግላዊ ውሳኔ ናቸው፡፡

ውጫዊ ተነሳሽነት ደግሞ ሌላኛው ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት በመምህራን፣በወላጆች እና በጓደኞች ወይም በሌላ አካል ለመወደስ፣ ለመሸለም'፣ ለመመስገን፣ በፈተና ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ እና ጥፋትን ቀንሶ ቅጣት ለማስቀረት የመሳሰሉ የአጭር ጊዜ ግቦችን የሚያስገኝ የተነሳሽነት ዓይነት ነው፡፡Stern፣ (1994). Noels (2003). Chtterrjee, (2000). አክለው ውጫዊ የመነሳሳት ባህርያት ከግለሰቡ ከራሱ ውጭ ከሆነ አካል ምላሽ ያስገኛሉ ተብለው የሚገመቱ ናቸው፡፡ ውጫዊ ምላሾች የሚባሉት ገንዘብ ሽልማት ማርክና አዎንታዊ ግብረ-መልሶች ናቸው፡፡ በመሆኑም ታላሚውን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ማጥናቱ በተለያዩ ተመራማሪዎች የተጠቀሱትንና ለስኬት መጥፋት መንስኤ የሚሆነውን ችግር በማቃለል የተማሪዎችን ስኬታማነት ወደፊት ያራምዳል፡፡ ተነሳሽነትና የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ተዛምዶን አስመልክቶ በተለምዶም ቢሆን ከተማሪዎች የትምህርት አቀባበል ባህሪይ መረዳት እንደሚቻለው አንድ ተማሪ በቋንቋ ትምህርት ፈተናው ጥሩ ውጤት የሚያስመዘግበው ታላሚውን ቋንቋ የመማር ምኞት ሲኖረውና ተሽሎ ለመገኘት ጥረት ሲያደርግ ነው እንዲህ አይነቱ ተማሪ በቋንቋው የመጠቀም ጥሩ ችሎታም ይኖረዋል ተብሎይገመታል፡፡

በዓለም ላይ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከትምህርት ውጤት ጋር የሚኖረውን ዝምድና ለመፈተሽ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ በመስኩ ቀዳሚነት እንዳላቸው የሚገመቱት Gardner, and Lambert ,(1972). በአሜሪካዊያን ዐውድ ውስጥ

ከእንግሊዝኛ ወይም ከፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ በመጡትና የፈረንሳይኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናሙናዎችን ወስደው የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተለዋዋጮችንና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ በሚመለከት ምርምር አካሂደዋል በውጤቱም የቋንቋ ተሰጥኦ የተነሳሽነት መጠንና የፈረንሳይኛ ቋንቋን ለመማር ያለ ምኞትን በተመለከተ ከተጠኝዎች በተገኘው መረጃ የተጠቀሱት ተለዋዋጮች ከትምህርት ውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ዝቅተኛ እንደሆነ ተገልፆዋል፡፡

ከውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት አይነቶች ውስጣዊ ተነሳሽነት በቋንቋ ትምህርት ውጤታማ እንደሚያደርግና በተለይም ለረጅም ጊዜ ትውስታ አስፈላጊ መሆኑን ተመራማሪዎችን (ዶርኔይ 1998፤ ዶርኔይና ሲዛር 1998፤ ክሩክስና ስኬሚድት 1991፤ ብራውንን 1990) በማጣቀስ ብራውን (2000) ያስረዳሉ፡፡ በሌላም በኩል በኖኤልስ (2001) ዋቢነት ጁልኪ (1998)፤ዶርኔይ (1998፣ 1994b’ 1990)፤ ብራውን (1990) ካለፉት አስርት ዓመታት ወዲህ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ይበልጥ ለማሳደግ ውስጣዊ ተነሳሽነት ትኩረት እያገኘ መምጣቱንና ከውጫዊ ይልቅ ውስጣዊ ተነሳሽነት ብልጫ እንዳለው አመላክተዋል፡፡ ኖኤልስ (2001) ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የጭንቀት መጠናቸው ዝቅተኛ ይሆናል፤ ስለሚማሩት ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ይኖራቸዋል፤ እንዲሁም ቋንቋ የመማር ብቃታቸውም ይጨምራል፤ በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሀርመር (2001) እና Ellis (1997) ውስጣዊ ተነሳሽት ከሌሎች የተነሳሽነት ዓይነቶች ይልቅ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታማ ያደርጋል፤ በሚል ሀሳቡን ያጠናክራሉ፡፡ በኦክስፎርድና ሽሪን (1996) ዋቢነት ፒንትሪችና ሽንክ (2002) እና Gardner ና Tremble (1994a) ውጫዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ቁሳዊ ሽልማትን ተስፋ በማድረግ ስለሚሠሩ ሽልማቱ ሲቋረጥ የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ይቀንሳል፤ በሚል ይህን ዓይነት ማበረታቻ አይደግፉም፡፡ ማበረታቻን ተስፋ ከማድረግ ይልቅ ተማሪዎቹ በራሳቸው ተነሳሽነት ቢማሩ ውጤታማ እንደሚሆኑ በመግለፅ ተመራማሪዎቹ የውስጣዊ ተነሳሽነትን ጠንካራ ጎን ያጎላሉ፡፡

በአጠቃላይ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን አማርኛ የመማር ተነሳሽነት ማጥናት የተማሪዎቹን ስነ-ልቦናዊ ችግሮችን በማቃለል ውጤታማ የሚሆኑበትን ሁኔታ ከማመቻቸት አንፃር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ክንውን ተማሪዎችን በቋንቋ ትምህርቱ ውጤታማ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ተነሳሽነት ነው Littlewood,(1981)፡፡ በዚህም ምክንያት ከተነሳሽነት ውጭ ግብ መቹና አጥጋቢ ውጤት ተግባራዊ ሊሆን አይችልም ይላሉ፡፡

ከአስተያየቱ ለመረዳት እንደሚቻለው ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ተሳታፊነት እንዳላቸው ከተግባራቱም ተጠቃሚ ለመሆን ተነሳሽነቱ የተሻለ ዕድል እንደሚፈጥርላቸው በተቃራኒው ደግሞ ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች በተግባራቱ በብቃት እንደማይሳተፉና በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርታቸው ደካማ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸው ይስተዋላል፡፡ Gardiner (1985) ተነሳሽነት በአመለካከቶችና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ የሚያመቻች ነው፡፡ የሚለውን መላምት ለማረጋገጥ ከሁለት አካባቢዎች መረጃ ሰብስበው ባካሄዱት ጥናት የተነሳሽነት ተጽእኖዎች ወይም አላባውያን በጥናቱ በማይካተቱበት ጊዜ በአመለካከት ልኬታዎችና በትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረው የተዛምዶ መጠን እንደሚቀንስ ወይም ጉልህነት እንደሌለው በተጨማሪም የአመለካከቶች ልኬታዎች ባልተካተቱበት ሁኔታ በተነሳሽነትና በቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረው ተዛምዶ ተጽእኖ ሊደርስበት የማይችል ስለ መሆኑ ተብራርቷል፡፡በሌላ መልኩ ደግሞ በመስኩ ከተካሄዱት የምርምር ስራዎች መካከል እያንዳንዱ የተነሳሽነት ዓይነት ከትምህርት ውጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ካመላከቱት የምርምር ውጤቶች በ Brannon (2000) የተጠቀሰው በ Gardner & Lambert (1972) በበፊሊፒንስ የተካሄደ ጥናት ነው፡፡ በምርምሩ Gardner & Lambert የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ሲያሳዩ የነበረው ጥረት ከእንግሊዝኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ውህደት ለመፍጠር ሳይሆን በቋንቋው ጥቅማጥቅም ለማግኘት እንደነበር Brown (2000) ያስረዳሉ፡፡

በኢትዮጵያም፣ ክፍሌ (2002 ዓ.ም.)፤ዘሪቱ(2008ዓ.ም) ተስፋዬ(2014ዓ.ም) አለምነሽ (2001 ዓ.ም.) አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በመማር ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ጥናት አድርገዋል፡፡

- በአለም አቀፍም ሆነ በሀገራችን በተደረጉ ጥናቶች  በተነሳሽነትና በትምህርት ውጤት መካከል አነሰም በዛ ተዛምዶ መኖሩ ተመላክቷል፡፡
- በመሆኑም አጥኚዋ በምትሰራበት ት/ቤት የሚገኙ ተማሪዎች አብላጫዎቹ አፋቸውን በ ኦሮምኛ የፈቱ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን የአማርኛ ቋንቋ ት/ት ውጤታቸው ዝቅተኛ መሆኑ እንዲሁም ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎትም በሚፈለገው ልክ አለመሆኑን በረጅም ግዜ ቅኝት የታዘበችው ጉዳይ ነው፡፡
- በተጨማሪም ከማስተማር ተመክሮ ለመረዳት እንደተቻለው ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የተማሩ የአብዛኞቹ ተማሪዎች ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህም ምናልባት ለውጤታቸው መቀነስ አንደኛው ምክንያት ተነሳሽነት ይሆን? የሚል ጥያቄ ለማንሳት ግድ ብሏል፡፡
- ለዚህም መፍትሄ ፍለጋ የውጤት መቀነሱ ከተነሳሽነታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ ለማጥናት እንደ ዋነኛ ምክንያት ሆኑዋል፡፡

## 1.3 የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ተማሪዎችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ቋንቋን ለማስተማር የተነሳሽነታቸውን መጠን ማወቅና ከትምርት ውጤታቸውም ጋር ተዛምዶ መኖር አለመኖሩን እየፈተሹ ተገቢውን እርምጃ መውሰዱ አስፈላጊ በመሆኑ አጥኚዋ የሚከተሉትን መሪ ጥያቅዎች እንደ መነሻ በመጠቀም ጥናቱን አካሂዳለች፡፡

1. በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?

2. የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዋና አላማ

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል የአፋን-ኦሮሞ አፌ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነትንና ውጤት ተዛምዶን መመርመር ነው፡፡

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- ተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለመማር ያላቸውን ተነሳሽነት መመርመር፡፡
- የተማሪዎቹ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት ያለውን ተዛምዶ መፈተሽ

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ጠቀሜታአማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የመፍቴ አቅጣጫ ማስቀመጥ እና ከዝያም በተጨማሪ በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ማስተማር ሂደት በተነሳሽነት እናበቋንቋ ትምህርት መካከል ስለሚኖረው ተዛምዶ ለማወቅ እና ከዝያም በተጨማሪ ተጠቃሚ መሆን ለሚፈልጉ ተማሪዎች ፣ መምህራን እና ተመራማሪዎች ጠቃሚ መረጃ መስጠት ይችላል ::ከዚህም ባሸገር ስረአት ትምህርት ቀራጨች እና ለመማሪያ መፅሐፍት አዘጋጆች ከስራቸው በፊት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ስለሚያጎለብቱ ክንውኖች ከግምት እንዲያስቡ እና መረጃ በመስጠትሊያግዙ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ሁለተኛ ቋን ቋ ትምህርት እና በተነሳሽነት ዙርያ የሚካሄደው ጥናት ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ወደፊት ይህንን ርእሰ አስመልክቶ ለሚደረጉ ምርምሮች መነሸ መሆን ይችላል ::ባጠቃላይ የዚህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የተነሳው የተማሪዎች ውጤት እና ተነሳሽነት አቸውን አስመልክቶ መረጃን በአግባቡ

በመመርመር የሚታዩትን ችግሮች ለይቶ ለሚመለከተው አካል በሙሉ ትክክለኛ መረጃመስጠት እና በተገኘው ውጤት ሁሉም ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በ2015 ዓ.ም በጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ ቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

በጥናቱ ሂደት ውስጥ የመማር ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤት የሚሉ ሁለት ተለዋዋጮች ገብተውበታል፡፡ የመማር ተነሳሽነት ነፃ ተለዋዋጭ ሲሆን የትምህርት ውጤት ደግሞ ጥገኛ ተለዋዋጭ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት የተማሪዎች ውጤት ተነሳሽነት በመኖሩ ወይም ባለመኖሩ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ነው፡፡

ጥናቱ የሚከተለው ተዛምዷዊ ስልት ነው፡፡ ምክንያቱም ያለው (1998) እንደገለፀው ተዛምዷዊ ጥናት በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ተለዋዋጮች መካከል ሊኖር የሚችልን የግንኙነት አቅጣጫና መጠን ለመወሰን የሚያስችል ስለሆነ ነው፡፡

ጥናቱ በዋናነት ውስጣዊ' ውጫዊ' ውህዳዊ እና ጥቅማ ጥቅማዊ በሚስኙት የተነሳሽነት ዓይነቶች ላይ የሚያተኩር ሲሆን ዕነዚህ ቋንቋን የመማር የተነሳሽነት አይነቶች እርስ በርሳቸው ያላቸው ተዛምዶ፤ከውጤት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ዕንዲሁም ከአራቱ የተነሳሽነት አይነቶች ውጤትን በመወሰን ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ ያለውንም መለየት የዚህ ጥናት ዐቅጣጫ ነበር፡፡

## 1.7. የቁልፍ ጽንሰ ሀሳቦች አጠቃቀም ብያኔ

1. *ተዛምዶ (Correlation)* ፡- የአፋን ኦሮሞ አፈ-ፈት ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ባላቸው ተነሳሽነትና በውጤታቸው መካከል የሚኖርን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ግኑኙነት ይመለከታል፡፡

*2. ተነሳሽነት፡-* የአፋን ኦሮሞ አፌ-ፌት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ሲማሩ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው አመለካከት፣ ፍላጎት፣ ስሜት፣ ጉጉት፣ ምኞትና ጥረት ይመለከታል፡፡

3. *የትምህርት ውጤት (Achievement):-* አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የአፋን ኦሮሞ አፌ-ፌት ተማሪዎች የሚኖራቸውን የተነሳሽነት መጠንና አይነት ተከትሎ በቋንቋው ፈተና ያስመዘገቡትን ውጤት ወይም ስኬት ይመለከታል፡፡

*4. ውሳጣዊ ተነሳሽነት፡-* የአማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና በቋንቋው ለመግባባት እንዲችሉ የሚያደርግ ውስጣዊ ወይም ተፈጥሮአዊ የመገፋፋት ስሜት ሲታይባቸው ውስጣዊ ተነሳሽነት ይባላል፡፡

*5. ውጫዊ ተነሳሽነት፡-* አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው እንዲያውቁ፣ እንዲረዱና ለመግባባት እንዲችሉ በሚያደርጉ ውጫዊ ጥቅሞች አማካይነት ቋንቋውን ለመማር የሚያሳዩትን የመገፋፋት ስሜት ይመለከታል፡፡

*6. ውህዳዊ ተነሳሽነት፡-* በተነሳሽነት መለኪያ መሠረት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ባህል ጋር ለመተሳሰር ያላቸውን ፍላጎትና ጥሩ አመለካከት ይገልጻል፡፡

*7. ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት፡-* በተነሳሽነት መለኪያ መሠረት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለተለያዩ ተግባራዊ ምክንያቶች ለምሳሌ፡- ስራ ለማግኘት፣ ፈተና ለማለፍ፣ እንዲሁም በቋንቋው ትምህርታዊና ኢኮኖሚያዊ አጋጣሚዎችን ለመጠቀም ቋንቋውን ለመማር የሚያሳዩትን ጥረት ይወክላል፡፡

*8. የጽሁፍ መጠይቅ፡-* በጽሑፍ ደረጃ ሊያዝ የሚችል አስተማማኝ የሆነ ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን የሚቆጥብ የመላሾችን ማንነት የማይገልጽ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. ጽንሰ ሀሳባዊ ቅኝት

### 2.1.1 የተነሳሽነት ጽንሰ-ሀሳብ ታሪካዊ አመጣጥ

Bolles (1967) የተነሳሽነት ንድፈ -ሀሳብ በሚለዉ ለሥራዉ ያስቀደመዉን ሀሳብ ሲጠቅስ የተነሳሽነት ጽንሸ ሀሳብ ስሜት ሊኖረዉ  የሚችለዉ በታሪካዊ ሀሳብ ሲቃኝ ነዉ፡፡የ Bolles አባባልን የሚደግፉ ተነሳሽነት በሚለዉ ርዕስ ዙሪያ ሰፊ የሆኑ ጽሑፎችና ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ እዚህ ላይ ታሪካዊ ለዉጥ በሆነ ሀሳብ ዉስጥ ሊገነዘቡት የሚችሉት የትኩረት ነጥብ ተቀምጧል ፡፡አጠቃላይ አንድን ነገር ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ የመረዳት ሂደት በስራ ላይ የዋለዉ በ( Bolles 1957) እና evans(1975) ሲሆን የተነሳሽነትን ታሪካዊ አመጣጥ  ከተናሳሽነት አስተሳሰብ ጋር የማገናኙቱ ሁኔታ አስተሳሰባቸዉን ለአሁን ዘመን እምነት እንዲጣልበት እንደ ዋና ምንጭ ይሆናል ፡፡

በመጀመሪያ kuethe(1958) ስለተነሳሽነት የሚለዉ ቃሉ መነሻዉ ላቲን እንደሆነ እና ያም ማለት በተለያየ አቅጣጫ መንቀሳቀስ ሲሆን አንድ ሰዉ ግቡን ላማሳካት የተነሳሳ ከሆነ በአብዛኛዉ ወደ ግቡ ይንቀሳቀሳል ይላል፡፡ በጥንቱ ዘመን የግሪክ ፈላስፋዎች Bolles (1967) እንደጠቀሰዉ የአንድ ሰዉ ችሎታ ምክንያን መቃኘት ለባህሪዉ ወሳኝ የሆነ ነዉ ፡፡ እንደ ፕላቶ እና ሶቅራጥስ አገላለጽ ባህሪ ከሁለት ነገሮች ‹‹ስሜት›› ወይም ‹‹እዉነት›› በአንዱ ሊወሰን ይችላል ፡፡ ስሜትን ከእንስሳት  እዉቀትን ከሰዉ ልጅ ባህሪ ምክነያቶችን በመጠቀም ተጋርቷል፡፡ evans(1975) በተጨማሪ የሰዉ ልጅ ችሎታ እዉቀትን ለማግኘት እንደነበር ግልጽ አድርጎ ሰዉ ተረድቷዋል እና የመልካምነት ስኬት እንደ ሆነ ጠቅሷል፡፡የግሪክ ፈላስፋዎች ስለተናሳሽነት እዉቀት ባበረከቱ አስተዋጸኦ ላይ ሀሳብ ሰጥቷል ፤ Bolles (1967) የሚመለከተዉ ጽፏል፡፡ ፕላቶ ፤ለአብዛኛዉ የግሪክ ፈላስፋዎች ባህሪን የሚወስኑ ተነሳሽነቶችን በመጠኑም ከሰዉ ባህሪ ጋር ግኑኝነት ስላላቸዉ መጥቀስ እንችላለን ምክንያቱም ሁልጊዜ ለሰዉ ችሎታ አስፈላጊ በመሆናቸዉ ፡፡ በችሎታዉ ምክንያት ሰዉ ንቁ ምክንያታዊ እንደ ነበር ተድርጎ ይታይ ነበር፡፡ እንደ

ምክንያታዊ ጭምር ፤ማድረግ የሚፈልገዉን ነገር ለመፈፀም በቂ የሆነ ምክንያት እንዲዘጋጅ ያደርገዋል ፡፡

Bolles (1967) Descartes (1694) ጠቅሶ እንስሳት ሲታሰቡ ምክንያታዊ የሆነ ሀሳብ እንደሌላቸዉ አሳይቷል ፡፡ በተጨማሪ የእንስሳትን ባህሪ በዉጫዊና ዉስጣዊ ኃይል ድርጊትን ለመፈጸም እንደሚያግዝ ገምቷል ፡፡ዉጫዊ አካላትን ለመቀስቀስ ዉስጣዊ ኃይል በቀስቃሽነት ይወክላል ፡፡ ሰዉ ምክንያቱን በግባትና በዉጤት መካከል በማስገባት ከእዉቀቱ አንጻር ነጻ ሆኖ ባህሪዉን ለመወሰንና ለመምራት አስችሎታል፡፡ Hobbes የhedonism የሥነ-አእምሮአዊ ጥናት አይነት አቅርቧል ፤ የተነሳሽነት ንድፍ-ሀሳብ በ18ኛ እና በ19ኛዉ ምዕትዓመት ዉስጥ የበላይነት ይዞ ነበር ፡፡ እንደ እሱ ሰዉ ድርጊት ለመፈጸም የሚነሳሳዉ ከሚያገኘዉ ጥሩ ነገር አንጻርና አስቸጋሪ የሆኑ ነገሮችን አንድ ጊዜ ሊያስወግድ ነዉ፡፡ በ hedonism አስተሳሰብ አስተሳሰብ ጋር ተቃርኖ ነበር ፡፡ ከጠቀሰዉ የሥነ-ምግባር መልካምነት የሰዉ ዝንባሌ ደስታን ለመከታተል እና ሀዘንን ለማስወገድ ከሚለዉ ጋር ነበር፡፡

John lock ድርጊቶችን ለመፈጸም በሚያነሳሱ ድርጊቶች ያለመረጋጋት እና ሚና ላይ ትኩረት አድርጎ ነበር ፡፡ እንደ lock እና hume ሁለቱም ሙከራዎች የሚተገበሩ ናቸዉ ፡፡ የማሰብና የመመራመር ችሎታ ተለዋዋጮች በከፍተኛ ደረጃ በሌሌች ተለዋዋጮች ላይ ጫና አድርገዋል ፡፡(madsen 1968):: hume በተጨማሪ የተመለከተዉ ልዩ ስሜቶችና ፍላጎቶች ሰዉ ድርጊቶችን ለመፈጸም የሚያደርጉ መሰረቶች ናቸዉ የሚለዉን ሀሳብ ነዉ፡፡

Hutstheson (1726)ሥነ-አዕምሮአዊ hedonism በቀላሉ ሁለት አይነት መነሳሻ ያቀረባቸዉን ደግፏል ፡፡ግላዊ ሆነ መነሳሻ የአንድን ሰዉ ደስታ ብቻ ይጠብቃል ፤ለሌላ ሰዉ አሳቢ መነሳሻ የሌላን ሰዉ ደስታ ይጠብቃል ፡፡ በኋላ እንደ (madsen 1968) Kantየመጀመሪያ ሰዉ ነበር ፡፡በሥነ-አዕምሮአዊያን አከፋፈል መገንዘብ ፣መገፋፋት ፣ፍላጎት ብሎ በተመሳሳይ ደረጃ የከፋፈላቸዉ የሶስትዮሽ ክፍፍሉ ከዚህ ምዕትዓመት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን በሥነ-አዕምሮ ላይ የበላይነቱን ተቀዳጅቷል፡፡በዚህ ክፍፍል የተነሳሽነት ተለዋዋጮች በሁለት ይከፈላሉ መገፋፋትና ፍላጎት በሚል፡፡

የሀሳቡ ተፈጥሮ የነበረዉ በጣም ዉጤታማ የሆነ አነሳሽ ኃይል እንደነበር በ Darwin እና spencez ተነግሯል። በሁለቱ ቁስ  አካላዊያን። ሁለቱም ተፈጥሯዊ ለሆነ ባህሪና ለተፈጥሮ የተነሳሽነት ንድፈ-ሀሳብ ላይ አጽንኦት ሰጥተዋል ። በዚህ ረገድ  Bolles (1967) ሲጠቅስ  አብዛኛዉ የእኛ የተነሳሽነት አስተሳሰቦች ከቁስ-አካላዊያን ላምዶች ጋር በብዙ መልኩ የተያያዙ ናቸዉ ። Darwin እና spencez የሚያካትቱ- Darwin የዘመናዊን ዘመን የተፈጥሮ ንድፈ-ሀሳብን አነቃቅቷል ። spencez የበለጠ ወሳኝ የሆኑ አስተዋጽኦችን አድርጓል--እሱ ለእኛ አብዛኛዉን ሕጎችን ለማጥበብ ተጨማሪ የሆነ ተዛማጅ ነገሮችን እና ለመማር ባህሪያዊ የሆኑ መገለጫዎችን ከራሱ ሀሳብ  አቅርቧል ። በማደግ ላይ ያለ የተነሳሽነት ንድፈ-ሀሳብ ማበረታቻን በማካተት።

M.daniel smith(1971) ተጨማሪ ሀሳብ አቀረበ።የሰዉ የባህሪ ለዉጥ እይታ ተቀባይነት አግኝቷል። የትኩረት አቅጣጫ ሊሆን የሚችለዉ አንዱ ለተነሳሽነት ምንጭ የሚሆነዉ ህይወት ያለዉ አካል እድገት ወይም አካባቢያዊ ተጽዕኖ ወይም እነሱ እራሳቸዉ አላማዎቻቸዉ ተፈጥሯዊ የሆኑ የተነሳሽነት ኃይል እንዲኖራቸዉ ሲፈልጉ የመሳሰሉ ናቸዉ።

Evans (1975) የሥነ-አዕምሮ ሳይንሳዊ ባህሪ ከ19ኛ ምዕትዓመት ዘግይቶ የምክንያቶችና የዋና ነገሮችን ሥርዓት አመቻችቷል። Mc dougal (1871-1938) የሰዉ ልጆች ባላቸዉ ተፈጥሮአዊ ፀጋ መመስገን ፣የሰዉ ልጆች ብዙ ተፈጥሯዊ ፀጋዎች አሏቸዉ። እስካሁን ግን በእንስሳት ዉስጥ እንዳለዉ በሰዉ ልጆች ዉስጥ ያለዉን ግትርነት አላረጋገጠም ። Evans (1975)ሀሳቡን ሲያቀርብ  በተናጠል የነበሩ የተፈጥሮ ፀጋዎች አንድ ላይ ሲሆኑ ሰዎች ሊያከናዉኗቸዉ የሚችሏቸዉ የተለያዩ ተግባትን እንዲፈጽሙ ለማሸቻል ተነሳሽነትን ያስገኝላቸዋል ።

### 2.1.2 የተነሳሽነት ምንነት

ተነሳሽነት የሚለዉን ስነ ልቦናዊ ጽንሠ ሃሳብ የተለያዩ ምሁራን በተለያየ መንገድ ብያኔዎችን ሲሰጡ ይስተዋላሉ፡፡ ከነዚህም ዉስጥ የሚከተሉት ተጠቃሽ ናቸዉ፡፡

Williams and burden (1997:120) እንደሚገልጹት ተነሳሽነት ንቁ በሆነ አእምሮ (በመሉ ንቃተ ሂሊና) እንድን ድርጊት ለመፈጸም የሚካሄድ ጥረትን የሚያበረታታ አእምሮታዊ እና ስሜታዊ ቅስቀሳ ነዉ፡፡

Brown (2000:160) የተነሳሽነት ምንነትን ከሚከተሉት እይታዎች አንጻር ብያኔአቸዉን ያስቀምጣል፡፡

- ተነሳሽነት ከባህሪያዉያን እይታ አንጻር አንድን ተግባር ለማከናወን ማጠናከሪያ ሰጥቶ ምላሽ እንዲሰጥ ከማድረግ ጋር የተያያዘ ነዉ ፡፡
- ከአእምሮታዉያን አኳያ በዚህ እይታ መሰረት ተነሳሽነት የሚመነጨዉ ከራሱ ከግለሰቡ ነዉ፡፡
- ይህ እይታ ከግንባታዉያን አንጻር በማህበራዊ አዉድ እንዲሁም በግለሰቦች ምርጫ ላይ የተመሰረተ ነዉ፡፡

ባጠቃላይ በሶስቱ መካከል ያለዉን የተነሳሽነት እይታዎችን Brown (2000:160) በሚከተለዉ መልኩ ያስቀምጡታል፡፡

በቋንቋ ትምህርት ሂደት ዉስጥ ሲታይ ለተማሪዉ ማበረታቻ ወይም ማጠናከሪያ እየተሰጠዉ የሚማር ከሆነ በባህሪያዉያን እይታ ተነሳሽነቱ ክፍተኛ እየሆነ እንደሚሄድ የሚያለክት ነዉ፡፡

በሌላ መልኩ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ያለምንም ዉጫዊ ተጽዕኖ በግለሰቡ ዉስጣዊ ፍላጎት ከፍ ዎይም ዝቅ ሊል ይችላል የሚሉት ደግሞ አእምሮያታዉያን ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም በግምባታዉያን አተያይ ተማሪዉ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ባለዉ ዉስጣዊ ተፅዕኖ እና በሚያከናዉነዉ ማህበራዊ ተራክቦ በተነሳሽነቱ ላይ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ መንገድ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

### 2.1.3 የተነሳሽነት አስፈላጊነት

ተነሳሽነት የሰው ሌጆች አንድን ተግባር እንዲያከናውኑ የሚያበረታታ ወይም የሚቀሰቅስ ከውስጣዊ ስሜት የሚፈልቅ ነው Brown (1994) Stipek (1996) Harmer (1991)፡፡

የዚህ ጠንካራ ውስጣዊ ስሜት ደግሞ ዋነኛ መሰረቱ ሰዎች በሚያከናውኑት ተግባር ላይ የሚኖራቸው ከልብ የመነጨ ፍላጎትና ለመስራት ያላቸው ጉጉት ነው፡፡ Curuzon (1984) በተመሳሳይ ሁኔታ የሌሎች ምሁራንን ሀሳብ በማጠናከር የራሳቸውን ሀሳብ ገልጸዋል፡፡ Farrant (1984) ተነሳሽነት ለትምህርት ካለው ፊይዳ ጋር በማያያዝ እንደገለጹት ተነሳሽነት አንድ ሰው ለመማር ከውስጡ እንዴት ተቀስቅሶ እንደሆነ የሚያመለክት ነገር ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ በአንዳች ምክንያት አነስተኛ የሆነ እንደሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተዳከመና ብቃት የጎደለው እንደሚሆን ያስረዳሉ፡፡ እኚሁ ምሁር ተነሳሽነት በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የጎላ ሚና እንዳለውና የግድ አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ለላይ ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ ተማሪዎች ለታላሚው ትምህርት ያላቸውን ውስጣዊ ስሜት ፣አመለካከትና በትምህርት ወቅት የሚሰጡትን ተግባራት ለመስራት ያላቸው ፍላጎት ወሳኝ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡

የሰው ልጆች በተሰማሩበት የስራ መስክ ወይም የሙያ መሰመር አልያም ሊያከናውኑ ለፈለጉት ተግባር የላቀ ስራ በመስራት ወደተፈለገው ውጤት ወይም ግብ ለመድረስ ተነሳሽነት አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ ተነሳሽነት ከውስጥ በሚመነጭ ፍለጎትና ግፊት ወደ ተግባር በመሰማራት የታቀደው አላማ ላይ ለመድረስ የሚያስችል በየትኛውም የስራ መስክ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ቁልፍ በሆኑ በትምህርት ስራ ላይም የሚኖረው ሚና ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም በቋንቋ ትምህርት የተማሪው ተነሳሽነት ቋንቋውን ከመማር አንስቶ እስከ መጠቀም ድረስ ባለው ሂደት ወሳኝነት አለው፡፡ እንዲሁም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚሰጠው ማንኛውም ትምህርት ተነሳሽነትን ሲያጎለብቱ ወደፊት ትምህርቱን ከተማሩ በኃላ በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ይገኛል ተብሎ ለታሰበው ግብ በቀላሉ መድረስ ይችላሉ፡፡ Gardner እና Lamberit (1959) ስለተነሳሽነት ሲገልጹ ተማሪው ሁለተኛ ቋንቋ ለመማር ካለው ዓላማ አንፃር እንደ አቀራረቡ ይገለፃል ይላሉ፡፡ ሁለት ዓይነት ተነሳሽነቶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ እነሱም ተዛምዶአዊና መሳሪያዊ ተነሳሽነቶች ናቸው፡፡

ተዘምዶአዊ ተነሳሽነት ተማሪው ለታለመው ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት እንዳለውና የታላሚውን ቋንቋ ባህል ለማወቅና የዚያ ማህበረሰብ አባል ሆኖ የመገኘትን ፍላጎት ያሳያል Csizer እና Dornyei (2005)፡፡

መሳሪያዊ ተነሳሽነት ቋንቋን ለመማር ቋንቋው እንዲያድግ ከፍተኛ የሆነውን ሚናን ይጫወታል (የሥራ ዕድል ለማግኘት ወይም የሥራ እድገት ለማግኘት ይጠቅማል)። Kouritzin፣ Piquemal እና Renaud (2009) ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ በራሳቸው እውን የሚያደርጉበት እና የራሳቸውንም የቋንቋ ብቃት የሚያሻሽሉበት ነው ይላሉ።

በራስ መወሰን ንደፈ-ሀሳብ ዕይታ Deci እና Ryan (1985) ሲገልጹ ተነሳሽነት ምን ያህል ተማሪዎች በሙሉ ፍላጎታቸው በድርጊቱ ለመሳተፍ እንደታጩ፣ ምርጫዎቻቸውና ስምምነቶቻቸው ላይ የተመሰረተ ሀሳብ ነው (Deci 1992)። በዚህ ሁኔታ ሁለት ዓይነት አቅጣጫዎች ሊቀመጡ ይችላሉ ( Deci እና Ryan 1985)።

በሥነ-አዕምሮያዊያን አቀራረብ ተነሳሽነት ሰዎች በልምዶቻቸው አማካይነት ከግብ ሊደርሱ የሚችሉበትን አቀራረብ እንዲመርጡና እነሱ ከመረጡት ሊገኝ የሚችለውን የውጤት ደረጃውን ይገልጻል (Keller 1983)። John stone (1999) ተነሳሽነት ልዩ የሆነ አላማን ለማሳካት የሚያነሳሳ ነው። በተመሳሳይ Ryna እና Deci (2000) ተነሳሽ መሆን ማለት ለውጥ ማምጣት ወይም አንድን ነገር ለመተግበር በእንቅስቃሴ ላይ መሆን ማለት ነው ይላሉ። Crump (1995) ለመማር ስሜት፣ ፍላጎት፣ ንቁነት፣ ትጋት የተነሳሽነት ዋና ክፍሎች ናቸው ብለው ያምናሉ። Louise (2011) እንደገለጹት ተነሳሽነት ለትምህርት ብቃት ትልቅ ሚና ይጫወታል። ተነሳሽነት ለሁለም ተማሪዎች በትምህርት ተግባር ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ሉያሳድር ይችላል። ተነሳሽነት ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡት ዝቅተኛ ውጤት ከሚያመጡ የሚለይ ዋነኛ ነገር ሊሆን እንደሚችል ይገልጻሉ።

ተነሳሽነት አንድን ተግባር የማከናወኛ ኃይል እንደሆነ የተለያዩ ምሁራን ሀሳባቸውን ይገልፃሉ። Ekrem (2012) እና Demir (2011)ን በመጥቀስ ተነሳሽነት አንድን የታሰበበት ዓላማ ለማሳካት ትልቅ ድርሻ ያለው መሆኑን ይገልጻሉ። እንዲሁም ግላዊ ተሳትፎን ለመጨመር እና ውጤታማ ለመሆን ያግዛል። Crookes እና Schmidt (1991) እንደሚሉት ተነሳሽነት የተማሪዎችን ቋንቋ ለመማር ያላቸውን ዝንባሌ የሚያሳይ ነው።

Mitra (2016) ተነሳሽነት አንድ ሰው አንድን ነገር ለማከናወን የሚያደፋፍር ወይንም ያለውን ዝንባሌ ለማሳደግ የሚያግዝ ነው። Tengku (2012) እና Jhonstone (1999) መነሳሳት ማለት አንድን ሥራ ለመስራት መንቀሳቀስ እንደሆነ ይገልጻሉ። በተጨማሪም

ሥራን ለመፈፀም የሚገፋፋ ወይም የሚያነቃቃ ነው። Keller (1983) እንደሚገልጹት ተነሳሽነት ሰዎች አንድን ተግባር መርጠውና ወደው የሚያከናውኑበት ልምምድ ወይም ለማከናወን ወይም ላለማከናወን የሚወስኑበት ነው።

ከላይ ከተገለጹት ከምሁራን ሀሳብ መገንzብ እንደሚቻለው ተነሳሽነት ማንኛውንም ተግባር ለማከናወን የሚገፋፋ አንዳች ኃይል መሆኑን መረዳት ይቻላል። ተማሪዎች ቋንቋን ለመማርና ተምረው ውጤታማ ለመሆን ያለላቸው ተነሳሽነት ወሳኝነት አለው። ሌሎች ተግባራትንም ተግብሮ ውጤታማ ለመሆን የግለሰቡ የተነሳሽነት መጠን ወሳኝነት ያለው ነው። እንዲሁም አንድን ሥራ ላለመፈፀም የምንወስንበት ሂደትም ተነሳሽነት ላይ መሠረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 2.1.4 የተነሳሽነት መገለጫዎች (ገጽታዎች)

በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተነሳሽነት የሚለው ስነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳብ ሲታሰብ በውስጡ ተያይዘው የሚነሱ ሌሎች ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች አሉ። Zimmerman & Bandura (1994) Pajares & Johnson (1996), Pajares & Valiente (1997) እና Payne (2012) እንደሚገልጹት ግለ ብቃት፣ ግለ ግንዛቤ እና ግለ መር ከተነሳሽነት ጋር ሊያያዙ የሚችሉ መገለጫዎች እንደሆኑ ያስረዳሉ። እነዚህን ሶስት ስነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች ምንነታቸውን በተመለከተ እንዲሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል።

#### 2.1.4.1 ግለ ብቃት (Self Eficacy)

ግለ ብቃት የተማሪዎችን የመጻፍ ተነሳሽነት ለመለካት ከሚያስችሉ የስነ ልቦና ገጽታዎች ውስጥ አንዱ ነው (Bandura:1986 እና Pajares: 2003):: ግለ ብቃት የሚለውን የስነልቦና ጽንሰ ሀሳብ የተለዩ ምሁራን ልዩ ልዩ ብያኔዎችን ሲሰጡት ይስተዋላል። ከእነዚህም መካከል Bandura (1986) እንደሚገልጹት ግለ ብቃት አንድን ተግባር በሚፈለገው መልኩ ከመፈጸም አኳያ የሚሰጥ ግለሰባዊ ውሳኔ ነው። በሌላ መልኩ የግለ ብቃት ምንነትን ከቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ Ehrman (1996:137)

እንደሚያስረዱት፣ ተማሪዎች በመማር ሂደት ላይ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመፍታት ያላቸው የመቋቋም ችሎታን የሚመለከት ነው፡፡

ከላይ የቀረቡት የግለ ብቃት ብያኔዎች በተጨማሪ ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው የግለ ብቃት ምንነትን በተመለከተ ሀሳባቸውን የሰነዘሩ ምሁራን አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ Pajares and Vialante (2006) እና Hashemenejad et al. (2014) ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንደ Pajares and Vialante (2006) አገላለጽ ግለ ብቃት በአጠቃላይ በመጻፍ ችሎታ ተማሪዎች የሚያሳዩት በራስ መተማመን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Hashemenejad et al. (2014) ከመጻፍ ትምህርት ጋር አያይዘው የግለ ብቃት ምንነትን እንደሚያስረዱት፣ ተማሪዎች ከመጻፍ ችሎታቸው ጋር በተያያዘ አለኝ ብለው የሚያምኑት አቅም/ብቃት ነው፡፡ እነዚህም የብቃት/የችሎታ አይነቶች ከመጻፍ ትምህርት ጋር የተያያዙ ንዑሳን ዓላማዎችን ከመጠቀም ጋር የሚያያዙ ሲሆን እነሱም፣ ድርሰት አድራጅቶ መጻፍን፣ ሥርዓተ ነጥብ በተገቢው ቦታ መጠቀምን፣ የታላሚውን ቋንቋ ፊደል በትክክል መጻፍን ፣ ሰዋስውን ጠብቆ የመጻፍ ተግባር ማከናወንን፣ ወዘተ…የሚጠይቁ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ግለ ብቃት አንዱ የተነሳሽነት ገጽታ ሲሆን፣ ተማሪዎች ቀደም ሲል ካከናወኗቸው ልዩ ልዩ የመጻፍ ተግባራት ተነስተው፣ በሂደት ከሚያሻሽሉት የመጻፍ ችሎታ አንጻር አለኝ ብለው ሊግልጹት የሚችሉት አቅም/ብቃት ነው፡፡

### 2.1.4.2 ግለ መር (Self Regulation)

ግለ መር ሌላኛው የተማሪዎችን የተነሳሽነት ደረጃ ለመለካት የሚያስችል እና የተነሳሽነት ወጤትን የሚያመለክት የስነልቦና ገጽታ ነው፡፡ የተለያዩ ምሁራንም ስለምንነቱ በተመለከተ ሀሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ Zimmerman (2008:166) እንደሚገልጹት ተማሪዎች በተለያዩ ዕለታዊ ገጠመኞች/ክንውኖች ያገኟቸውን አቅሞች (ቃላዊ አመለካከቶች) ወደ ስነትምህርታዊ ችሎታ ለመለወጥ ጥረት የሚያደርጉበት ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Pajares and Vialante (2006)

እንደሚያስረዱት በመጻፍ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች በግለ መር የመማር ብልሃት ተማሪዎች ዓላማዎችን ይነድፋሉ፤ መረጃዎችን ይሰበስባሉ፤ እቅድ ያወጣሉ፤ ያደራጃሉ፤ እንዲሁም ይገመግማሉ፡፡

በሌላ በኩል Shunk & Zimmerman (1994) እንደሚያስረዱት ራስን መምራት በቋንቋ ትምህርት አውድ ውስጥ ተማሪዎች ራሳቸውን የሚቆጣጠሩበት እና የሚገመግሙበት ሂደት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የተማሪዎች ግለ መርነት የመጻፍ ችሎታቸውን ይተነብያል ተብሎ ይታሰባል፡፡ በሌላ አገላለጽ የተማሪዎች የግለ መርነት ክህሎቶች በቋንቋ ትምህርት የሚሰሯቸውን ተግባራት በአወንታዊም ሆነ በአሉታዊ መልኩ ይተነብያሉ እንደማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ከተሰጡት ብያኔዎች መረዳት የሚቻለው ግለ መር ፣ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ራሳቸውን የሚቆጣጠሩበት እና የሚገመግሙበት ተግባር ሲሆን፣ በዚህ ሂደት ውስጥም ዓላማ ከመንደፍ አንስቶ አደራጅቶ እስከመገምገም ድረስ ልዩ ልዩ ሂደቶችን ያልፋሉ፡፡

### 2.1.4.3 ግለ ግንዛቤ (Self Concept)

ግለ ግንዛቤ እና ግለ ብቃት የሚሉት ሥነልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦች በተወሰነ መልኩ ተመሳሳይነት ይስተዋልባቸዋል፤ ሆኖም ዕይታቸው የተለየ መሆኑን የተለያዩ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል Pajares and Schunk (2001) እንደሚገልጹት ግለ ግንዛቤ በጥቅል አስተሳሰባዊ እምነቶች ላይ ትኩረት ሲያደርግ፣ ግለ ብቃት ግን ሊለኩ የሚችሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ከማከናወን አንጻር የሚታይ ነው፡፡ በተመሳሳይ Pajares (2003) እንደሚያስረዱት ግለ ግንዛቤ ተማሪዎች ለራሳቸው ያላቸውን አጠቃላይ ግምት የሚወስኑበት ሲሆን፣ ግለ ብቃት ግን ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ሂደት ውስጥ ካሉ ዝርዝር ዓላማዎች/ተግባራት አንጻር ያላቸውን ችሎታ የሚተነብዩበት ነው፡፡ ይህን በምሳሌ ስንመለከተው "በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ ጥሩ ጸሀፊ እንደሆንኩ ይሰማኛል" የሚለው ግለ ግንዛቤን ሲወክል፣"በምጽፍበት ጊዜ በአማርኛ ቋንቋ ሰፊ አግልግሎት

ያላቸውን ቃላት እጠቀማለሁ" የሚለው ደግሞ ግለ ብቃትን መሰረት ያደረገ የአጠያየቅ መንገድ ነው፡፡

በአጠቃላይ ግለ ብቃት፣ ግለ ግንዛቤ እና ግለ መር የሚሉት ስነልቦናዊ እሳቤዎች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የየራሳቸው ፋይዳ አላቸው፡፡ እነዚህም ጽንሰ ሀሳቦች የተለያዩ ቢሆንም፣ ከተማሪዎች የመጻፍ ተነሳሽነት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ከፍተኛ መሆኑ ያመሳስላቸዋል፡፡ በዚህ የጥናት ሂደትም የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለመለካት ሶስቱም ስነ ልቦናዊ ጽንሰ ሀሳቦችን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች ከተለያዩ ምሁራን ተወስደው ተግባር ላይ ሊውሉ ችለዋል፡፡

## 2.1.5 የተነሳሽነት አይነቶች

የሁለተኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነት ምርምር መሪ የሆኑት ጋርድነርና ላምበርት (1959) ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ውህዳዊና ጥቅማዊ በማለት በሁለት ይከፍሉታል (Gardener 2001፣ ብራውን 2000፣ Gardener 1985 እና Gardener 1982)፡፡ በዊሊያምስና ቡርደን (1997) ዋቢነት ቺክዘንትማሊና ናካሙራ (1989) ደግሞ ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት ዓይነቶችን አስተዋውቀዋል፡፡

*ዉህዳዊ ተነሳሽነት* የታለሚዉ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋዉ ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት ጋር ዉህደት ወይም ቅርርብ ለመፍጠር በማሰብ ቋንቋዉን ለመማር ወይም ለማጥናት የሚነሱበት የተነሳሽነት አይነት ነዉ፡፡Gardenr (1985) ተማሪዎቹ ቋንቋዉን የሚማሩት ከቋንቋዉ ተናጋሪዎች ጋር ዉህደት ለመፍጠር በመሆኑ ቋንቋዉን የመማር ተሳትፏቸዉ የተወሰነ ስርአተ ትምህርት ሲጠናቀቅ የሚቋረጥ እንደማይሆን Gardener(1985) ያብራራሉ፡፡

ሁለተኛዉ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተነሳሽነት አይነት ደግሞ *ጥቅማጥቅማዊ* ተነሳሽነት ነዉ፡፡ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚዉ ቋንቋ ተግባራዊ ወይም ተጨባጭ ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ቋንቋዉን የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት ነዉ Ellis.(1997) Gardener(1985)፡፡ ተማሪዎች ታላሚዉን

ቋንቋ የሚማሩበት አላማ የተለያዩ ቢሆንም በአብዛኛዉ ግን የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርት ማሟላት የተሻለ ክፍያ ወይም ደሞዝ ማግኘት፤አለማቀፋዊ መረጃና እዉቀት ማግኘት የሚሉት ዋና ዋና የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አላማዎች መሆናቸዉን Noris (2001) ያስረዳሉ፡፡

ሶስተኛዉ ዉስጣዊ የተነሳሽነት አይነት ነዉ፡፡ ዉስጣዊ ተነሳሽነት የሚባለዉ የተነሳሽነት አይነት በስነ ልቦና ትምህርት ዉስጥ ከብዙጊዜ ጀምሮ የታወቀ እንደሆነ Ellis (1994) ይገልፃሉ፡፡ዉስጣዊ ተነሳሽነት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ታላሚዉን ቋንቋ ከዉስጥ በሚመነጭ ግፊት የመማር ተግባራትን በማከናወን የሚገኝ የተነሳሽነት አይነት ነዉ፡፤

ተማሪዎች የመምህሩ የማስተማር ዘዴ ቢመቻቸዉም ባይመቻቸዉም ትምህርቱ ፈተና ቢኖረዉም ባይኖረዉም ቋንቋዉን ከመማር ወደኋላ አይሉም፡፡ ቋንቋዉን በመማር ሆነ ተግባራቱን በማከናወን ይረካሉ፡፡ ዉስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸዉ ተማሪዎች የሚቀርቡላቸዉ የመማር ተግባራት አሰቸጋሪ ቢሆኑም እንኳን ተግባራቱን በማከናወን ይደሰታሉ፡፡ዉጫዊ ማነሳሻ ወይም የመምህሩ ግፊትና ጉትጎታ ሳያስፈልጋቸዉ ከራሳቸዉ የሚመነጭ የመስራት ፍላጎት ይኖራቸዋል Noels ,(2003). Ur, (1996).

አራተኛዉ የተነሳሽነት አይነት ዉጫዊ ተነሳሽነት ነዉ፡ይህ በመምህራን ፤በወላጆች ፤በጓደኞች ወይም በሌላ አካል ለመወደስ ፤ሽልማት ለማግኘት ፤ለመመስገን ፤በፈተና ጥሩ ዉጤት ለማስመዝገብ ፤ጥፋት በመቀነስ ቅጣት ለማስቀረት ያሉ የአጭር ጊዜ ግቦችን የሚያስገኝ የተነሳሽነት አይነት ነዉ፡፡Elliot ,and others ,(2005).Brawon,(1994).

በአጠቃላይ በዘሪቱ(2003)፡፡ የተጠቀሱት Gardenere-(1985)እንደሚያስረዱት በሁሉም የተነሳሽነት አይነቶች አንድን ግለሰብ ተነሳስቷል ለማለት ሁለት ነገሮችን መሰረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡የመጀመሪያዉ ግለሰቡ አላማ ተኮር የሆነ እንቅስቃሴ ሲያሳይ ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ ግለሰቡ ጥረት የሚታይበት ከሆነ ነዉ፡፤በዚህ ሁኔታ ዉስጥ ያለ ግለሰብ ስለሚያከናዉኗቸዉ ተግባራት ቢጠየቅ ለዚሁ አላማ ያለዉን

ምኞት ወይም ፍላጎትና ቋንቋዉን መማር ለሚያስችሉ ተግባራቱ ያሉትን ጥሩ አመለካከቶች ያንጸባርቃል፡ ከዚህም በመነሳት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አራት ሁኔታዎችን ያካተተ ነዉ ለማለት ይቻላል እነዚህም ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ግብ ፤ጥረት የተሞላበት ባህሪ፤አላማን የማሳካት ምኞትና ለሚከናወነዉ ተግባር የሚኖሩ ጥሩ አመለካከቶች ናቸዉ Gardener(1985) አክለዉ እንደሚያብራሩት ከላይ የሰፈሩት ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት ሁኔታዎች ከፅንሰ ሀሳብ አኳያ በሁለት ምድቦች ይከፈላሉ፡፡

በክፍፍሉ የመጀመሪያው ምድብ ግብ ነው፡፡ ለተነሳሽነት ግብ ምክንያት ወይም የሚገፋፉ ነገር ቢሆንም በግለሰቦች መካከል ያለን መለያየት አያንፀባርቅም፤ከተነሳሽነት፡ አንፃርም ሊለካ፡ አይችልም ፤ ግብ የሚንፀባረቀው ፡ ግለሰቡ ሁለተኛ ቋንቋውን ለማጥናት በሚኖረው ዝንባቤ ነው፡፡ በሁለተኛው ምድብ የተቀመጡት ጥረት የተሞላበት ፡ ባህሪይ ' ዓላማን የማሳካት ምኞትና ለሚከናወነው ተግባር የሚኖሩትን ጥሩ አመለካከቶቶችን የሚመለከት ነው፡፡ በእነዚህ ሶስት ሁኔታዎች በግለሰቦች ማካከል ልዩነት ይንፀባረቃል፡፡ ሁኔታዎቹም በቀጥታ ሊለኩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ሁለተኛ ቋንቋ ፡ የመማር ተነሳሽነትን፡ መመርመር ከውህዳዊም፡ ሆነ፡ ከጥቅማጥቅማዊ የዝንባሌ ዓይነቶች ጋር ግንኙነት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም የሚችሉ ሶስት ውስብስብ ባህርያትን መመልከት ያስችላል፡፡ እነዚህ ውስብስብ፡ ባህሪያት ወይም ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አላባዉያን የሚባሉት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት የሚባሉት መጠን ወይም ጥረት ፤ ሁለተኛ ቋንቋውን የመማር ዓላማን የማሳካት ምኞትና ሁለተኛ ቋንቋውን፡ ለመማር የሚኖር ጥሩ አመለካከት ናቸው፡፡

### 2.1.6 ተነሳሽነትና የወደፊት ግብ ተዛምዶ

ተነሳሽነት ከመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ሂደትና ከተማሪዎች የወደፊት ግብ ጋር ግንኙነትና ዝምድና አለው፡፡ Henderkize (1975) ይህንን ሀሳብ ሲገልጹ ተነሳሽነት አንድን ድርጊት ለመተግበር የሚያበቃ እንቅስቃሴ እንደሆነና ከመምህሩና ከተማሪው

ተግባር ጋር በተያያዘ መልኩ መምህሩ ተማሪዎቹን እሱ በፈቀደ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ ካላደረገ በስተቀር በእቅዱ መሰረት ዓላማውን ሊያሳካ እንደማይችልና ይህን መሰሉ ተነሳሽነት በመማሪያ ክፍል ብቻ ተወስኖ የሚቀር ሳይሆን ተማሪዎችን ተከትሎ መሄድ እንዳለበት ያብራራል፡፡

እንዲሁም ተነሳሽነት ከተማሪዎች የወደፊት ግብ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው፡፡ ተማሪዎቹ የሚማሩት ትምህርት ለወደፊቱ ግባቸው አስተዋጽኦ የሚኖረው ከሆነ የመማር ፍላጎታቸው ይጨምራል፡፡ ይህ ካሌሆነ ግን ፍላጎታቸው አናሳ ይሆናል በማለት Wilkins (1978) ያብራራሉ፡፡ ተነሳሽነት ከተማሪዎች የወደፉት ግብ ጋር ያለውን ቀጥተኛ ተዛምዶ አስመልክቶ መሰሉ (1994) ይህንን ሀሳብ በማጠናከር እንዲህ ይገልጻሉ፡፡

> ተነሳሽነት ተማሪዎች ትምህርቱን ሲማሩ ከሚኖራቸው ግብ ጋር ይያያዛል፡፡ ግባቸው ዘለቄታ ያለው ከሆነ እዚያ ግብ ላይ ለመድረስ ሲለ በትምህርቱ ጠንካራ ተነሳሽ ይሆናል፡፡ ይህም ለዘለቄታው የስራ ዕድል ለማግኘትና ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ተግባብቶ ለመኖር እቅድ ያላቸውን ተማሪዎች ይመለከታል፡፡ በአንፃሩ ግብአቸው የውስንነት ባህሪ ካለው ተነሳሽነታቸው የተዳከመ ይሆናል፡፡ ይህም በትምህርትነት ስለተሰጠ ብቻ በአመቱ ማጠቃለያ ፈተናውን ለማለፍ መማርን ይመለከታል፡፡

ተነሳሽነት ከተማሪዎች የወደፉት ግብ ጋር ያለው ተዛምዶን በተመለከተ ግብአቸውን ለረጅም ጊዛ አቅደውት ከሆነ የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጠንካራና ዘለቄታ ያለው ይሆናል፡፡ ሆኖም በአጭሩ የሚያስቡና ከክፍል ክፍልe ለማለፍ በትምህርትነት ስለተሰጠ ብቻ ከሆነ ግን ተነሳሽነታቸው ደካማ ይሆናል፡፡

### 2.1.7 የተነሳሽነት መኖር አለመኖሩ የሚታወቅባቸው መንገዶች

ተነሳሽነት የሰው ልጆች አንድን ተግባር ለማከናወን ከውስጣቸው ፈንቅሎ የሚወጣ ውስጣዊ ስሜት እንደሆነ ባለፉት ክፍሎች አይተናል፡፡ ከዚህ የተነሳ በመማር ማስተማር ሂደትም ተማሪዎች ለሚማሩት ትምህርት ተነሳሽነት ይኑራቸው አይኑራቸው ማወቅ አእንደሚቻል መሰለ (1994) ገልጸዋል፡፡

## የተነሳሽነት መኖር

በተማሪዎች ዘንድ ተነሳሽነት መኖሩን ማወቅ እንደሚቻል የተለያዩ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ከነዚህም መካከል Kristen (1984) እና Curuzon (1984) ሲገለጹ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የተነሳሱበትን ትምህርት በአግባቡ የመማር ፍላጎታቸው ከፍተኛና ጠንካራ ነው፡: ይህም ሲባል ተማሪዎቹ ክፍለጊዜው ከተጀመረበት ሰዓት አንስቶ እስኪፈጸም ድረስ ትምህርቱን በተመስጦ ይከታተላሉ፣ በጥሞና ያዳምጣሉ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚሰጡ ማንኛውም የክፍል ውስጥ እንቅስቃሴ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፣ የተሰጣቸውን ስራ ሰርተው በታቀደው ጊዛ አጠናቀው ለማሳየት ከፍተኛ ጉጉት ይኖራቸዋል ይላሉ፡፡

በተጨማሪም ከመምህራን ጋር ጤነኛ የሆነ ቀረቤታ ይኖራቸዋል፣ የሚሰጣቸውን ስራ ሁሉ በሚገባ ተግባራዊ ለማድረግ ይጥራሉ ፣ለመምህራቸውም ሆነ ለትምህርቱ ቀና አመለካከት አላቸው በማለት ይገልጻሉ፡፡ Henderkize (1975) ይህንኑ ሀሳብ ሲያጠናክሩ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ከመምህራን ጋር በቀላሉ ይግባባሉ፣ በክፍል ውስጥ በተማሪዎችም ሆነ በመምህሩ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይጥራሉ፣ የመማሪያ መሳሪያቸውን በአግባቡ ይጠቀሙበታል፣ በመምህራቸው ላይ እምነት ስለሚኖራቸው በእሱ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ትምህርቶችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይቀበላሉ፣ተቃዋሚዎች አይሆኑም፣ ያለመሰልቸት የታዘዙትን ሁሉ ያከናውናሉ፡፡ ስለዚህ የተማሪዎች ተነሳሽነት መኖሩን ማወቅ የሚቻለው ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸው ፍለጎት ከፍተኛና ጠንካራ መሆኑን በክፍል ውስጥ በሚደረገው ማንኛውንም እንቅስቃሴ ንቁ ተሳታፉ ሆነው መገኘታቸው ነው፡፡

ሌዑልሰገድ (1999) እንደገለፀው አዎንታዊ ተነሳሽነት ያለው ተማሪ የሚከተሉት ባህሪያት ይንፀባረቁበታል፡-

- በቋንቋ ትምህርቱ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ
- በትምህርት ሂደት በውይይትና በክርክር በሚገባ ይሳተፋሉ
- ከመምህሩም ሆነ ከተማሪዎች የሚሰነዘር ሀሳብን በትኩረት ይከታተላሉ
- የሚሰጠውን የቤት ሥራ በተገቢው መንገድ
- አስፈላጊ የሆኑ የትምህርት መሳሪያዎችን ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ ያለውንም በአግባቡ ይጠቀማሉ
- ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ተባብሮ ለመስራት ፍለጎታቸው ከፍተኛ ነው
- በአስቸጋሪ (ፈታኝ) ጊዜም ውስጥ ነገሮችን በትዕግስት ያልፋሉ
- በመምህሩ የሚሰጡ የክፍል ውስጥ ተግባራትን በብቃት ለመሥራት ጥረት ያደርጋል ወዘተ

በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ዘንድ የተነሳሽነት መኖር አለመኖርን አስመልክቶ ተማሪዎችን ለማነሳሳት ምክንያት የሚሆኑ ነገሮችን መሠረት በማድረግ ተነሳሽነትን በሁለት ከፍሎ ማየት እንደሚቻል ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ይህም አዎንታዊ (ጠንካራ) ተነሳሽነትና አሉታዊ (ደካማ) ተነሳሽነት ናቸው፡፡

አዎንታዊ ተነሳሽነት አንድን ነገር በሚገባ ለማከናወን ከሚፈጠረው ውስጣዊ ደስታ ወይም ስሜት የሚፈጠር ነው፡፡ እንዲህ አይነት ተነሳሽነት አላማው ተማሪው አንድን ጉዳይ ለመተግበር በሚያደርገው ጥረት ደስታን ለመፍጠር ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሁሌጊዜ ሽልማት ወይም ምስጋና ለማግኘት አይደለም፡፡ ሆኖም ተማሪው በሚያሳየው እንቅስቃሴ ወይም ተሳትፎ በመምህሩ እንዲደነቅ ወይም እንዲበረታታ ይበልጥ ደግሞ በሚያገኘው ውጤት እርካታ ለማግኘት እንደሆነ Henderkize (1975) ይገልጻሉ፡፡

### ተነሳሽነት አለመኖር

ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች ተነሳሽነት ካላቸው ተማሪዎች ተቃራኒ የሆነ ባህሪይ ይታይባቸዋል፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚማሩት ትምህርትም ሆነ ለመምህራን ግድ የላቸውም፡፡ የሚታዘዙትንም ለመስራት ከውስጥ የመነጨ ፍላጎት

አይኖራቸውም፡፡ አዘውትረው በትምህርት ገበታቸው ሊይ አይገኙም በማለት Henderkize (1975) ያብራራሉ፡፡ Curuzon (1984) ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ንቁ ተሳታፊዎች ለመሆን የሚያስችላቸው ከውስጥ የሚገፋፋ ፍላጎት የላቸውም፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚፈጠሩ አንድአንድ የስነ ስርዓት ችግር ግንባር ቀደም ተሳታፊዎችና ቀስቃሾች እንደሚሆኑ ይገልጻሉ፡፡

ይህን ሀሳብ ሌዑልሰገድ(1999) እንደሚከተለው አስፍሮታል

- ተማሪው በሰዓቱ በክፍል ውስጥ አለመገኘት
- ወደ ክፍል ገብተው የመሰላቸት ሁኔታ ማሳየት
- መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ስለሚያነሱት ፍሬ ነገር ግዴ የለሽ መሆን በዚህም የተነሳ ማስታወሻ አለመያዝ
- ክፍለ ጊዛው ስለሚረዝምበት ተቁነጥናጭ መሆን
- ከቢጤዎቹ ጋር ተረዳድቶ ለመሥራት ፍላጎት ማጣት
- የትምህርት መሳሪያዎቹ እና የክፍል ውስጥ ተግባራቱ አሰልቺ መስሎ መታየት
- ያለበቂ ምክንያት በቡድን ሥራ ውስጥ አለመግባባትን መፍጠር፣ ችግሩን ለመቅረፍ አለመሻት
- አዳዲስ ተግባራትን ከመተግበር የተለመዱትን ብቻ መከወን
- አስቀድመው የተማሩትን አለማስታወስ ወዘተ

የተማሪዎች ተነሳሽነት አለመኖርን አስመልክቶ ተነሳሽነት አዎንታዊና ሉታዊ ተነሳሽነት በመባል በሁለት እንደሚከፈሌ ቀደም ብል ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሰረት የተማሪዎችን አሉታዊ ተነሳሽነት ከተነሳሽነት አለመኖር ጋር አያይዘው Henderkize (1975) ሲገልጹ አሉታዊ ተነሳሽነት ፍርሀትን ተከትሎ የሚመጣ ውስጣዊ ስሜት ነው ይላሉ፡፡
አንድ ተማሪ ትምህርቱን በትክክል ባለመከታተሉ ወይም ዝቅተኛ ውጤት በማምጣቱ መምህሩ ወይም ቤተሰቡ ሊያስከትሉበት የሚችሉትን ቅጣት በማሰብ ከሚከሰት

ፍርሃት የሚመነጭ ነው፡፡ በዚሁ መልክ የተነሳሳ ተማሪ ዓላማው ፈተናውን በጥሩ ውጤት ለማለፍ ብቻ እንጂ ትምህርቱን በጥለቀት ለማወቅ አስቦ የሚነሳሳ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነቱ ተነሳሽነት ተማሪው ዋነኛ ትኩረቱ ታላሚውን ቋንቋ ለመዳ ላይ ሳይሆን ፈተና ለማለፍ ብቻ በመሆኑ የታለመው ወይም የሚፈለገው የአሰራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ላይመጣ ይችላል፡፡ ሌላው ለአሉታዊ ተነሳሽነት ምክንያት የሚሆነው ግብ ሳይኖራቸው ወደ ክፍል የሚመጡ ተማሪዎች ናቸው፡፡ እነዙህ ተማሪዎች ለትምህርት ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ በተለይም በቋንቋው አፍ የፈቱ ተማሪዎች ከሆኑ ቋንቋውን እናውቃለን የሚል እምነት ስለሚኖራቸው የስነ ሌቦና ዝግጅት ስለሌላቸው ለትምህርቱ ተነሳሽነት የላቸውም፡፡ ይህም አሉታዊ ተነሳሽነታቸውን ያጎላዋል፡፡

### 2.1.8 በተነሳሽነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ነገሮች

በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ተነሳሽነት ሊይ ተጽዕኖ የሚያሳዴሩ በርካታ ጉዲዮች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ አመለካከት፣ የመምህሩ ሁኔታ፣ የመማሪያ ክፍል ሁኔታና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**ሀ. አሉታዊ አመለካከት**

የሰው ሌጆች ለተለያዩ ነገሮችና ጉዳዮች የሚኖራቸው ስሜት ጥሩ ወይም መጥፎ አስተያየት ነው፡፡ Chapman (1991) ይህንን አመለካከት ሰዎች ከብጤዎቻቸው ፣ከቤተሰቦቻቸው ፣ ከማህበረሰቡና ከመሳሰለት ጋር በሚያደርጉት ተራክቦ ይዘውት ያደጉት አመለካከት በተለያዩ አጋጣሚዎች አዱስ ከሚገጥማቸው ገጠመኞች ጋር ሳይጣጣም ሲቀር ወይም ቀደም ሲል ለአንድ ነገር የነበራቸው ግምት ዝቅተኛ ሆኖ ሲያገኙት የሚከሰት እንደሆነ Atkins (1996) ያስረዳሉ፡፡

አለማየሁ (1995) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሶ የተማሪዎችን የመውደድ ወይም የጥላቻ ስሜት ሲገሌጽ የተደረሰበት ውሳኔ የመውደድ ከሆነ ሰውዬው በነገሩ አዎንታዊ አመለካከት ይኖረዋል፡፡ የጥላቻ ከሆነ ደግሞ አሉታዊ አመለካከት ይኖረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ውሳኔ ፀንቶ እስከመጨረሻ የሚቆይ ላይሆን ይችላል ይላል፡፡ አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ አመለካከት በታላሚው ቋንቋ ትምህርት ሂደት በተማሪዎች

ተነሳሽነት ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተጽዕኖ እንዳለው Brown (1994)ን በመጥቀስ አለማየሁ (1995) ያብራራሉ፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ላይ አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ያላቸው ከሆነ ለመማር ተነሳሽነት ይኖራቸዋል፡፡ አሉታዊ ከሆነ ደግሞ ተነሳሽነቱ የቀነሰ ይሆናል፡፡ እንደዚህ አይነት አመለካከት ካላቸው በቋንቋ ለመmዳ ወቅት ለማጁ ቋንቋውን ይጠላዋል እያደገ ሲሄድም ይህንኑ ባህሪ ያጎላል፡፡

ይሁንና የዚህ አይነቱን ሁኔታ መምህሩ ሲገጥመው በቸልታ ማለፍ የለበትም፡፡ የተማሪዎችን አመለካከት ለመቀየር ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ያለበለዚያ ከታሰበው ግብ ለመድeረስ ይከብዳል፡፡ Brown (1994)ን በመጥቀስ ሺበሺ (1994) ተነሳሽነትና አመለካከት ጥብቅ ትስስር እንዳላቸውና ተነጣጥለው የሚታዩ ጉዳዮች እንዳይደሉ ፤በተማሪው ተነሳሽነት ላይ አመለካከት ትልቅ ድርሻ እንዳለው ይገልጻሉ፡፡ ተማሪው ለሚማረው ትምህርት ጥሩ አመለካከት ካለው በትምህርቱ ሂደት ጥሩ ተነሳሽ ይሆናል፤ አሉታዊ አመለካከት ካለው ደግሞ ተነሳሽነቱ ዜቅተኛ እንደሚሆንም ያብራራሉ፡፡

### ለ. የመምህሩ ሁኔታ

የመምህሩ ሀኔታ ከተማሪው ተነሳሽነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እንዳለው Ceoftrey (1978) ይገልጻሉ፡፡ መምህሩ ትምህርቱን ለማስተማር በቅድሚያ እራሱ ተነሳሽ ሆኖ በበቂ የትምህርት ዝግጅት የሚያስተምር ከሆነ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖራቸውና ተነሳሽነታቸው እንዲጎለብት ማድረግ እንደሚቻልም አክለው ያብራራሉ፡፡ የመምህሩ ሁኔታ ከቋንቋ ትምህርት ጋር እንደሚያያዝ BYren(1976) በቋንቋ ትምህርት ሂዯት መምህሩ ተማሪው ለትምህርቱ ተነሳሽ እንዲሆን ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል ይላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን የፈቀደውን ያህል ቢለፋ ልፊቱ በሙሉ መና እንደሚሆን ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም መምህሩ ተማሪዎችን ለትምህርቱ ተነሳሽ ማድረግ የሚችለው

በአንድ ጊዜ ሳይሆን በሂደት አስፈላጊውን የማነሳሻ ብልሀት ተጠቅሞ እንደሆነ Curuzon (1984) ይገልጻል፡፡

በተጨማሪ አንድ መምህር ተማሪዎቹ እንዲኖራቸው የፈለገው አይነት ተነሳሽነት እስኪፈጠር የትምህርት ጊዜውን ማባከን የለበትም፡፡ ተማሪዎቹ ለጊዜው የያዙትን ተነሳሽነት እንደያዙ ቀስ በቀስ የተፈለገውን አይነት ተነሳሽነት ማምጣት እንደሚችሉ Curuzon (1984) ይገልጻል፡፡ BYren (1976) ለተነሳሽነት መፈጠር ዋናው ነገር መምህሩ የትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ መምህሩ የተማሪዎችን ፍላጎትና ችሎታ ከግንዛቤ በማስገባት ቀደም ብሎ ማራኪ ፣አዝናኝና ሳቢ እንዲሁም ሁሉንም ተማሪ ሊያሳትፍ በሚችል መልኩ መልመጃዎችን በመቅረጽ ቢቀርብ የተነሳሽ ተማሪዎችን መጠን ይጨምራል፡፡ ሌላው መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ያለው ቀረቤታ ነው፡፡ የቋንቋ መምህር ጥሩ ስነምግባር የተላበሰ እንደአባትም እንደወንድምም እየሆነ ተማሪዎቹን በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት ለተነሳሽነት ሚና ትኩረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ተነሳሽነትን ማሳደግ፣ ማጠናከር ያስፈልጋል፡፡ ተነሳሽነት ቋንቋን በመማር ማስተማር ረገድ ለጠቃሚነቱና ለውጤታማነቱ ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡ በትክክል መምህሩ ለተማሪዎች ያለው የአመለካከት እውቀትና በመማር ማስተማሩ ሥራ የተካነ ከሆነ የቋንቋ መምህሩ በጣም ጠቃሚ የሆነና ውጤታማ ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡

ተነሳሽነት ከፍተኛ ሥነ-ልቦናዊ ወይም ማህበራዊ ፍላጎት ነው፡፡ መምህሩ ዓላማውንና ፍላጎቱን ከግብ ለማድረስና ስኬታማ ለመሆን ያስችለዋል፡፡ የተነሳሽነት መጠኑና ዓይነቱ ለመማር ማስተማሩ ሂደት በጣም አስፈላጊ እና ወሳኝ የሆነ ሚና ይጫወታል፡፡ በተጨማሪ የቋንቋ መምህሩ ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ተነሳሽነቱ እንዲኖራቸው የማድረግ ሚና አለው፡፡

በተማሪዎች ዘንዴ ሁለት አይነት ተነሳሽነቶችን ማየት ይቻላል፡፡ እነርሱም ከፍተኛ አመለካከት ጠቃሚ፣ ብቃትና ጠቃሚ ውጤት ያለውና ሁለተኛው ዜቅተኛ አመለካከት ቋንቋን እንዲይማሩ ተጽዕኖ የሚያደርግ እና በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ደካማ መሆን ናቸው፡፡

እንደ Brophy (2004) አገላለጽ የትምህርት ማህበረሰብ በተማሪዎች ተነሳሽነት ሊይ ቁልፍ የሆነ ጉዳይ ነው፡፡ ከትምህርት ማህበረሰብ ውስጥ አንዱ መምህር ሲሆን ለአብነት መምህሩ ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ መመለስ መቻል አለበት፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች እርስ በእርስ መማማር እና ስህተታቸው በራሳቸው ማረም እንዲችሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ መምህሩ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ እንዲሁም የዚህ ተግባር ምሳሌ መሆን አለበት፡፡ ብዙ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ተማሪዎች ውጤታማ የሆነ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው የትምህርት ማህበረሰብ ትኩረት ማድረግ ያለባቸው ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ አንደኛው መምህሩ ለትምህርቱ እራሱን ማዘጋጀት አለበት፡፡ ሁለተኛው ለሚያስተምረው ትምህርትና ለሚያሳካው ዓላማ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ እንዱሁም ተማሪዎችን በመማር ማስተማር ሂደት ማገዝ መቻል አለበት፡፡

Donyei (2001) እንደገለጹት በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ መምህሩ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሳሌ፡- የመምህሩ የድምጽ ጥራት እና ትምህርቱን ለማስተማር ያለው ተነሳሽነት አዎንታዊ መሆን የተማሪውን ተነሳሽነትን ለመጨመር ያግዛል፡፡ በተቃራኒው አሉታዊ ሲሆን ደግሞ ተነሳሽነታቸው እየቀነሰ ይመጣል፡፡ በተጨማሪ የመምህሩ ውጤት፣ እምነት፣ ፀባይ፣ ሁኔታ እንዲሁም ከተማሪው ጋር ያለው መልካም ግንኙነት፣ የትምህርት ደረጃውና የትምህርት ዓይነት በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር የሚችሉ እና በብዛት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ የተጠቀሱ ነገሮች አዎንታዊ ከሆኑ የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚጨምሩ ሲሆን አሉታዊ የሚሆኑ ከሆነ ደግሞ ተነሳሽነታቸውን የሚቀንሱ ይሆናሉ፡፡

**ሐ. የመማሪያ ክፍል ሁኔታ**

በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች አንዱ የመማሪያ ክፍሎች ሁኔታ ነው፡፡ Harmer(1991) እንዳስገነዘቡት የመማሪያ ክፍሎች ውስጣዊ እና ውጫዊ አደረጃጀት በተማሪዎች ላይ እራሱን የቻለ ተጽዕኖ አለው፡፡ የመማሪያ ክፍሎች ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺና ተማሪዎቹ እርስ በእርሳቸው ለሚያደርጉት ተራክቦ ምቹ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ የተማሪዎች ቁጥር ከክፍሉ አቅም

በላይ መሆን የለበትም፡፡ ከአቅም በላይ ተማሪዎች የታጎሩበት ከሆነ ትምህርቱን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት አነስተኛ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከክፍሉ ጋር የተመጣጠነ የተማሪ ቁጥር ፣በቂ የፀሀይ ብርሃንና አየር የሚያገኝ ፣ ንጽህናው የተጠበቀ ክፍል ከሆነ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት እንዲጨምር የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

Mitra (2016) Macintyre (1999)ን በመጥቀስ እንደሚለት ምቹ የመማሪያ ክፍል መፍጠርና የተማሪዎችን ምቾት መጠበቅ ቋንቋውን ለመማር የሚኖራቸውን ተነሳሽነትን ከፍ ለማዴረግ አስተዋጽኦ አለው፡፡ Mitra (2016) Good እና Brophy (1994)ን በመጥቀስ እንደገለጹት ደግሞ ምቾት በሌለው የመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለማሳደግ ያስቸግራል፡፡ መምህሩም ለሚያስተምረው ትምህርት ስኬታማነት አይኖረውም፡፡ የተሳካ የቋንቋ መማር ማስተማር ምቹ የመማሪያ ክፍልና ነፃነት የሚሰማቸው ተማሪዎች ሊሆኑ ይገባል፡፡ የመማሪያ ክፍል ምቾት የሌለው ከሆነ እንዱሁም ተማሪዎች ነፃነት የማይሰማቸው ሲሆን ቋንቋን ለመማር ባላቸው ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ በሌላ መልኩ ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ባላቸው ተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የተለያዩ ምክንያቶች ይኖራሉ፡፡እነዚህም ተጽዕኖዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

Ditual (2012፣ 63) ተማሪዎች ቋንቋን ለመማር ተነሳሽ ሲሆኑ ለቋንቋው ጥሩ አመለካከት ይኖራቸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት ያመቻል፡፡ Chang (2010) በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ብዛት ሲኖር እና የሚጨናነቁ ከሆነ ተነሳሽነታቸው እየቀነሰ ይመጣል፡፡ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ተሳትፎ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ ስለዚህ በክፍል ውስጥ ያለው የተማሪ ብዛት በተነሳሽነት ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

### መ. የትምህርት መሣሪያዎች

የተማሪዎችን የትምህርት መሣሪያን በተመለከተ የትምህርት መሳሪያዎች በባለሙያ በጥንቃቄ የሚዘጋጁ ነገሮች ናቸው፡፡ በተለይም የተማሪዎች የመማሪያ መጽሀፍት

ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ናቸው፡፡ አንድ የቋንቋ መምህር የመማሪያ መጽሀፍትን ከመጠቀሙ በፊት ከተማሪዎች የቀደመ እውቀት ጋር መጣጣሙን ማረጋገጥ እንዳለበት Burmbaugh /1997/ ይገልጻሉ፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት የመማሪያ መሳሪያዎች የሚጫወቱት ሚና የላቀ ነው፡፡ በተለይም የመማሪያ መጽሀፍት ጠቀሜታ የሚታወቅ ቢሆንም በቀጥታ ግልጋሎት ላይ ከመዋሉ በፊት መምህሩ ዜግጅቱ ምን ያህል ተማሪውን ይመጥነዋል የሚለውን ማወቅ እንዲለበት Harmer (1991) ይገልጻል፡፡ የተማሪዎች የመማሪያ መጽሀፍት ዝግጅት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚሻ ስራ በመሆኑ የተማሪውን ትኩረት የሚስቡ ከችሎታቸውና ከፍላጎታቸው ጋር የተጣጣሙና የተመጣጠኑ መሆን እንዳለባቸው ሺበሺ (1994) ሴልስ ሙርሺያን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ በአጠቃላይ ከገለጻው መረዳት የሚቻለው የመማሪያ መጽሀፍ ዜግጅት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ልምድና ችሎታ ያላገናዘበ ፍላጎታቸውን ያልዳሰሰ ከሆነ ተነሳሽነታቸውን ሊጎዳ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

### ሰ. የማህበረሰብ ተጽዕኖ

በተማሪው ተነሳሽነትና አመለካከት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት ውስጥ አንዱ ማህበረሰብ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለትምህርት በሚቀርበው ቋንቋ እና በቋንቋው ተናጋሪዎች ላይ ያለው እይታ አሉታዊ ከሆነ፣የተማሪዎች ጓደኞች ቋንቋውን የሚያጥላሉና በቋንቋው ለመግባባት ጥረት የማያደርጉ ከሆነ፣ለቋንቋው መምህራቸው ቀና አመለካከት የሌላቸው ከሆነ እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ተማሪ ለቋንቋው ተነሳሽ እንዳይሆንና አሉታዊ አመለካከት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

### ረ. ቋንቋዎች ከታለሚው ቋንቋ ጋር ያላቸው ቅርበት

ተማሪው አፍ የፈታበት ቋንቋ እና ታላሚው ቋንቋ የአንድ ቋንቋ ቤተሰብ አባል ካልሆኑ ትምህርቱን ለመረዳት ስለሚከብዳቸው ለቋንቋው ጥሩ የሆነ ተነሳሽነትና አመለካከት አይኖራቸውም፡፡ በተነሳሽነት ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ተነሳሽነትን በተመለከተ ብዙ ምሁራን ለተነሳሽነት ምንነት ሆነ ተነሳሽነት በትምህርት ላይ የሚኖረውን በጎም ሆነ ተነሳሽነት ከሌለ ደግሞ መጥፎ ገጽታን

ለማሳየት ሞክረዋል ፡፡ ስለተነሳሽነት ሲታሰብ አንድን ነገር ለመፈጸም (ለማድረግ) ውስጣዊ የሆነ ተነሳሽነት ካለ ውጤታማ የመሆን እድሉ በጣም ሰፊ ነው፡፡

ተነሳሽነት እንዲኖር ለነገሮች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖር ያስፈልጋል፡፡ አዎንታዊ አመለካከት ከሌለ ተነሳሽነት አይኖርም፣ ተነሳሽነት ከሌለ ለነገሮች ያለ አመለካከት አሉታዊ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በማንኛውም የትምህርት አይነት ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ካስፈለገ በተማሪዎች ዘንድ ውስጣዊ ተነሳሽነትና አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖር ግድ ይላል፡፡

## 2.2 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በቢፍቱ ጊቤ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015ዓ.ም 10ኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት እና ከውጤታቸው ጋር ያለውንም ተዛምዶ መርምሮ የመፍትሔ ሀሳብ ለመስጠት ነው፤ በመሆኑም ከጥናቱ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተዛማጅነት ያላቸው በሀገር ውስጥና በውጭ ምሁራን የተካሄዱ ቀደምት ጥናቶችን በሚከተለው መልኩ ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

እያንዳንዱ የተነሳሽነት ዓይነት ከወጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ያመላከቱ ጥናቶችም አሉ፡፡ በጋርድነርና ላምበርት (1972) በፊሊፒንስ የተካሄደው ጥናት በቀዳሚነት ይጠቀሳል (ብራውን 2000፤ ኤሊስ 1994)፡፡ በዚህም የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ያሳዩት ጥረት ከእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ጋር ውህድት ለመፍጠር ሳይሆን በቋንቋው ጥቅም ለማግኘት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ጋርድነርና ላምበርት ከፊሊፒንሱ የጥናት ግኝታቸው በመነሳት በጥቅማዊ ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን በስኬት መማር እንደሚቻል አመላክተዋል (ብራውን 2000፤ ኤሊስ 1994)፡፡ በሌላ በኩል ኖሪስሆልት (2001) እና ብራውን (2000) የጠቀሷቸው ሉክማኒ (1972) ጥቅማዊ ዓላማ ያላቸው በህንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የማራቲ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች እንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር ብቃታቸው መጎልበቱን አመላክተዋል፡፡ ብራውን (2000)

እንደሚያስረዱት በጥቅሉ ሲታይ ህንድ ውስጥ ከጥቅማዊ ዓላማ ውጭ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጤታማ መሆን የተለመደ አይደለም፡፡

የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የትምህርት ውጤት ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ለመማር በሚኖራቸው የተነሳሽነት አይነት እና መጠን የሚወሰን እንደሆነ የተለያዩ ተመራማሪዎች ያመላክታሉ፡፡Ellis, (1995). (1994).Garediner, (1985)፡፡ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የሚማሩበት የራሳቸው የሆነ አላማ ይኖራቸዋል፡፡ካላማዎቹ ዋና ዋናዎቹ ከታላሚዎቹ ቋንቋዎች ከተናጋሪዎች ጋር ማህበራዊ ውህደት ለመፍጠር ካልሆነም በቋንቋው ጥቅማ ጥቅም ለማግኘት ለምሳሌ ፤ስራ ለመቀጠር፤ንግድ ለመነገድ ወዘተ ያሉ ናቸው፡፡

በተመሳሳይም Noels,(2001). የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ገጽታ በመደነቅ ፤ወዳጅነት ለመፍጠር፤ አእምሯዊ ችሎታን ለመፈተሽ ወዘተ አላማዎች ሲሉ ታላሚዉን ቋንቋ በተሳካ ሁኔታ ሊማሩ እንደሚፈልጉ ይገልጻሉ፡፡

ሁለተኛ ቋንቋን የሚማሩበት ሌላው ገጽታ ሽልማት ለማግኘት ለመመስገን ወዘተ አላማዎችም ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን እንደሚማሩ Noels, (2001). Brown, (1994).stern, (1994).ያብራራሉ፡፡

Gurdner (2001) ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን ውህዳዊ እና ጥቅማጥቅማዊ በማለት ይከፍሉታል፡፡ ውህዳዊ ተነሳሽነት ፡-የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት ጋር ቅርበት ለመፍጠር በማሰብ ቋንቋውን ለማጥናት የሚነሳሱበት የተነሳሽነት አይነት ነው፡፡ ይህም ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋና ባህል መልካም አመለካከት ስለሚኖራቸው ከዚሁ በመነሳት ቋንቋውን ለመማር የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጠንካራ እንደሚሆን ይስተዋላል፡፡

ሌላው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ነው፡፡ ተማሪዎች በጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አብዛኛውም ጊዜ የዩኒቨርሲቲ መግቢያ መስፈርት ማሟላት፤የተሸለ ደሞዝ ወይም ክፍያ ማግኘት ፤አለማቀፋዊ መረጃ እና እውቀት ማግኘት የሚሉት ዋና ዋና የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት አላማዎች መሆናቸውን Noris, (2001).ያስረዳሉ፡፡

ይሁን እንጂ ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ካላቸው እና ውህዳዊ ተነሳሽነት ካላቸው ተማሪዎች የትኞቹ ታላሚዉን ቋንቋ በተሻለ ይማራሉ? ለሚለው ጥያቄ የተለያየ ሃሳብ ሲሰነዘርበት ቆይቷል፡፡gardener & lambert, (1972). አብዛኛውን ጊዜ ከጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት የበለጠ ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ቋንቋውን በተሻለ ሁኔታ ይማሩታል የሚል እምነት እንዳላቸው Ellis, (1995). &Estern, (1994). ይገልጻሉ፡፡

ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ቋንቋውን በመማር ሂደት ለረጅም ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የመማር ስኬት ይኖራቸዋል፡፡ በዚህም ተማሪዎቹ ከታላሚው ቋንቋ ማህበረሰብ አባላት ጋር በመዋሀድ ማህበራዊ መስተጋብር ፈጥረው የመኖር ፍላጎት ስለሚያድርባቸው ቋንቋውን የመማር ተነሳሽነታቸው የላቀ ነው ፡፡ከዚሁ ጋር በተያያዘ በ Noris, (2001). የተጠቀሱት finigan, (1999). ውህዳዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች የአፊ-ፊቶችን የመሰለ ንበት የመጠቀም ችሎታ ሁሉ አላቸው በማለት የውህዳዊ ተነሳሽነትን ብልጫ ሲያወድሱ ክፍሌ (2002) ግን ሃሳቡ የተጋነነ ይመስላል በማለት ሲተቹ ይስተዋላሉ፡፡ለዚህም የሚያቀርቡት ምክንያት ምንም እንኳን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች በጎ አመለካከት ቢኖራቸውም የቋንቋውን ተናጋሪዎች የመሰለ የቋንቋ አጠቃቀም ወይም ንበት መጠቀም ይችላሉ የሚለው ሃሳብ አጠራጣሪ ስለሚሆን ነው የሚል ነው፡፡

እንደ ውህዳዊ እና ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ሁሉ ተደጋግመው የሚነሱት ሌሎች የተነሳሽነት አይነቶች ውስጣዊና ውጫዊ የተነሳሽነት አይነቶች ናቸው Noels, (2001). Brown, (2000). የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከውስጥ በሚመነጭ ግፊት ሁለተኛ ቋንቋን በመማር ተግባራትን በማከናወን የሚገኝ የተነሳሽነት አይነት ነው፡፡ የመምህሩ የማስተማር ስልት ለተማሪዎቹ ቢስማማም ባይስማማም፤ትምህርቱ ፈተና ቢኖረውም ባይኖረወም ቋንቋውን ከመማር ወደኋላ የማይሉበት ነው፡፡በቋንቋው ትምህርት እና በተግባራቱ ክንዋኔ እርካታ ያገኛሉ፤የውስጣዊ ተነሳሽነት ተማሪዎች የሚቀርቡላቸው የመማር ተግባሮች ምንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆኑ እንኳን ተግባራቱን በማከናወን ይረካሉ፡፡የውጭ ግፊትና ጉትጎታ ሳያስፈልጋቸው ከራሳቸው የሚመነጭ የመስራት ፍላጎት ያላቸው ናቸው፡፡Noels, (2003).

በውስጣዊ ተነሳሽነት ቀጥሎ የሚነሳው ሌላኛው የተነሳሽነት አይነት ውጫዊ ተነሳሽነት የሚባለው ነው፡፡ ውጫዊ ተነሳሽነት በሚፈጠርበት መንገድና በግቡ ውጤት ከውስጣዊ ተነሳሽነት ይለያል፡፡ በጓደኞች፡ በወላጆች፤ በመምህራን ወይም በሌላ አካል ለመወደስ ፤ለመሸለም፤ለመመስገን ፤በፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ፤ ጥፋትን ቀንሶ ቅጣት በማስቀረት የመሳሰሉ ያጭር ጊዜ ግቦችን የሚያስገኝ ነው፡፡ Elliot. &others (2005) Noelse, (2003). ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲቀንስ ውጫዊ ተነሳሽነት ተጽዕኖ የሚያሳርፍበት ሁኔታም አለ፡፡

Pintriche, (2002). እንደተመራማሪዎቹ አመለካከት በውስጣዊ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት ለሚከናወን ተግባር ውጫዊ የሆኑ ሽልማቶች ሲሰጡ ውስጣዊ ተነሳሽነት እንዲቀንስ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

በክፍሌ (2002) የተጠቀሱት Devis,(1999) እንደሚያስረዱት ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ራሳቸውን ይችሉ ዘንድ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ተከታታይነት ያለው፤ወቅታዊ የሆነ፤የተማሪዎችን እምነት አጠናክሮ በደንብ እንዲሰሩ የሚያስችል አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በጣም ቀላል ፤ በጣምም ከባድ ያልሆኑ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች ስኬታማ የሚሆኑባቸውን አጋጣሚዎች ማመቻቸት፤ከሚቀርቡላቸው የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ የሚያንጸባርቁ ትርጉሞችን እንዲፈልጉ ማድረግ፤ በራሳቸው የሚተማመኑ፤ዋጋ ያላቸው ጠቃሚ የትምህርት ማሃበረሰብ አባላት መሆናቸው እንዲሰማቸው ሞራላቸውን መጠበቅና ውስጣዊ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ማድረግ አለባቸው ይላሉ፡፡

Gardenre, (2003). ተነሳሽነትና ውጤታማነት እርስ በእርሳዊ ቁርኝት እንዳላቸው ሲያስረዱ ellis, (1995) ደግሞ ዝቅተኛ ተነሳሽነት ዝቅተኛ ውጤትን ፤ዝቅተኛ ውጤትም እንደገና መልሶ ዝቅተኛ ተነሳሽነትን እንደሚያስከትል አመላክተዋል፡፡

Gardiner (1985) እንደሚያብራሩት ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትን መመርመር ከውህዳዊም ሆነ ከጥቅማጥቅማዊ የዝንባሌ አይነቶች ጋር ግንኙነት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም የሚችሉ ሦስት ውስብስብ ባህርያትን መመልከት ያስችላል፡፡እነዚህ

ውስብሰብ ባህሪያት ወይም ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት አላባዊያን የሚባሉት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን የመማር አላማን የማሳካት ምኞትና ሁለተኛ ቋንቋውን ለመማር የሚኖር ጥሩ አመለካከት ናቸው፡፡

በመስኩ ቀዳሚ የሆኑትና በብራውን (2000፣ 1994)፣ በኤሊስ (1994) እና በጋርድነር (1985) ዋቢ ከተደረጉት ከጋርድነርና ላምበርት (1959፣ 1972) ጀምሮ ሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነትንና የውጤት ተዛምዶን የፈተሹ ምርምሮች በካናዳ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ ተካሂደዋል፡፡ በጋርድነር (1985) የተጠቀሱት ጋርድነርና ላምበርት (1959)፣ ጋርድነር (1960) አመለካከትና ተነሳሽነት ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ያላቸው ተዛምዶ ምን ያህል እንደሆነ ለመመርምር ፈረንሳይኛን በሁለተኛ ቋንቋነት በሚማሩ ተማሪዎች ላይ ተመሳሳይ ጥናቶችን አድርገዋል፡፡ በሁለቱም ተከታታይ ጥናቶች መካከል ልዩነት ታይቷል፡፡ በጋርድነርና ላምበርት (1959) ጥናት ተላውጦዎቹ 14 ሲሆኑ፣ ተሳታፊዎቹ 75 የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከ14ቱ ተላውጦዎች አራቱ ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ትኩረት የተሰጣቸው ሲሆኑ ከእነዚህም ሁለቱ (የቋንቋ ተሰጥኦና ተነሳሽነት) ከፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት ጋር ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡ በጥናቱ ተነሳሽነትን ያመላከቱ ተላውጦዎች የፈረንሳይኛ ቋንቋ ቃላዊ ውጤት፣ ዝንባሌ፣ ለቋንቋው ተናጋሪዎች ያለ አመለካከትና የተነሳሽነት መጠን ናቸው፡፡ በተንባይ ስታትስቲክስ በተሰላው ውጤት መሠረት በውህዳዊ ዝንባሌ፣ ለቋንቋው ተናጋሪዎች ባለ አመለካከትና በተነሳሽነት መጠን መካከል ግልፅ የሆነ ተዛምዶ ታይቷል፡፡ ከጋርድነርና ላምበርት (1959) በተለየ ጋርድነር (1960) ዘጠኝ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ብቃትን የሚለኩ መልስ አስመራጭ መለኪያዎችን በማካተት፣ የአመለካከት ልኬታዎችን ቁጥር ከፍ በማድረግና ፍላጎት የሚለውን የተነሳሽነት አላባ ለመለካት እንዲቻል በጥናታቸው እንደአንድ የአመለካከት አላባ የተመደበውን ፈረንሳይኛን ለመማር ያለ ምኞት በማካተት የጋርድነርንና ላምባርትን ጥናት በሞንትሪያል ያስፋፉ መሆኑን ጋርድነር (1985) ያስረዳሉ፡፡ በጥናቱም የፈረንሳይኛ ቋንቋ ብቃት ልኬቶች ከቋንቋ ተሰጥኦ ወይም ችሎታ፣ ከአመለካከትና ከተነሳሽነት ተላውጦዎች ጋር ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡

በአሜሪካዊያን አውድ ውስጥ ከእንግሊዝኛ ወይም ከፈረንሳይኛ ተናጋሪ ማህበረሰብ በመጡና ፈረንሳይኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ከሚማሩ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናሙናዎችን በመውሰድ በብራውን (2000፣ 1994) እና በጋርድነር (1985) የተጠቀሱት ጋርድነርና ላምበርት (1972) ባካሄዱት ጥናትም የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተላውጠዎችንና የውጤት ተዛምዶ መርምረዋል፡፡ በዚህም የቋንቋ ተሰጥኦ፣ የተነሳሽነት መጠንና ፈረንሳይኛን ለመማር ያለ ምኞትን በተመለከተ ከተሳታፊዎች የተገኘው መረጃ የተጠቀሱት ተላውጦዎች ከትምህርት ውጤት ጋር ዝቅተኛ ተዛምዶ አሳይተዋል፡፡ ከዚህም ሌላ በተወሰኑ ናሙናዎች ላይ የተነሳሽነት ማመላከቻዎች ከፈረንሳይኛ ትምህርት ውጤት ጋር ዝቅተኛ ተዛምዶ እንደታየባቸው፣ ሁለት የተነሳሽነት ማመላከቻዎች ከየትኛውም የአመለካከት ተላውጦ ጋር ግልፅ የሆነ ተዛምዶ ያልታየባቸው ስለመሆኑ ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በውስን ናሙናዎች ላይ የተነሳሽነት ተላውጦዎች ከወላጅ ድጋፍ ጋር፣ በተወሰኑ ናሙናዎች መሠረት ደግሞ ሁለት የተነሳሽነት አላባዎች ከዝንባሌ ጋር ግንኙነት እንዳላቸውም ተረጋግጧል፡፡ በተወሰኑ ናሙናዎችም የትምህርት ውጤት ተማሪዎች ለፈረንሳይኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ካላቸው በጎ አመለካከት ጋር ግንኙነት እንዳለው ተረጋግጧል፡፡

Gardner(1985) የጠቀሷቸው ጋርድነር፣ ስሚቴ፣ ክሊመንትና Gliksman(1976) ከ7ኛ እስከ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ከእያንዳንዱ የክፍል ደረጃ ወካይ ናሙናዎችን በመውሰድ በተለያዩ የሁለተኛ ቋንቋ መማር ንዑሳን ተላውጦዎች፣ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤቶችና የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ለመቀጠል ባለ ፍላጎት መካከል ያለውን ተዛምዶ በተንባይ ስታትስቲክስ ለክተዋል፡፡ ተዛምዶው ከመሰላቱም በፊት የውጫዊ ተፅዕኖ አድራሽ ተላውጦዎችን ተፅዕኖ ለማስወገድ መረጃዎቹ በቡድኖቹ መካከል ደረጃቸውን የጠበቁ (መደበኛ) እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ በስሌቱም መሠረት ከክፍል ተሳትፎ ውጤት፣ ደረጃቸውን ከጠበቁ ጥሩ የጽሑፍ ፈተናዎች፣ ከቃላዊ ብቃት ማመላከቻዎች አንፃርም ቢሆን ተነሳሽነትና የቋንቋ ተሰጥኦ ጥሩ የሁለተኛ ቋንቋ ብቃት ተንባይ ሆነዋል፡፡ ሁለተኛ ቋንቋውን ለመጠቀም የሚኖሩ አጋጣሚዎችን ከመጠቀምም ሆነ በቋንቋ ጥናቱ ለመቀጠል ካላቸው አስተሳሰብ አንፃር ተነሳሽነት ከቋንቋ ተሰጥኦ በተሻለ ሁኔታ ጥሩ ተንባይ መሆኑም በጥናቱ ተጠቁሟል፡፡

ጋርድነርም (1979) በጋርድነር (1985) ዋቢነት ተነሳሽነት በአመለካከቶችና በትምህርት ውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ አመቻች ነው፤ የሚለውን መላምት ለማረጋገጥ ከሁለት አካባቢዎች መረጃ በመሰብሰብ መርምረዋል፡፡ በጥናቱም የተነሳሽነት ተፅዕኖዎች ወይም አላባዊያን በጥናቱ በማይካተቱበት ጊዜ በአመለካከት ልኬታዎችና በትምህርት ውጤት መካከል ያለው ተዛምዶ በጣም እንደሚቀንስ ወይም ጉልህ እንደማይሆን፣ እንዲሁም የአመለካከቶች ልኬታዎች ባልተካተቱበት ሁኔታ በተነሳሽነትና በትምህርት ውጤት መካከል የሚኖረው ተዛምዶ ተፅዕኖ የማይደርስበት ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እያንዳንዱ የተነሳሽነት ዓይነት ከወጤት ጋር ያለውን ተዛምዶ ያመላከቱ ጥናቶችም አሉ፡፡ በጋርድነርና ላምበርት (1972) በፊሊፒንስ የተካሄደው ጥናት በቀዳሚነት ይጠቀሳል (ብራውን 2000፤ ኤሊስ 1994)፡፡ በዚህም የፊሊፒንስ ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ብቃታቸውን ለማሳደግ ያሳዩት ጥረት ከእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ጋር ውህድት ለመፍጠር ሳይሆን በቋንቋው ጥቅም ለማግኘት እንደነበር ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ጋርድነርና ላምበርት ከፊሊፒንሱ የጥናት ግኝታቸው በመነሳት በጥቅማዊ ተነሳሽነት ሁለተኛ ቋንቋን በስኬት መማር እንደሚቻል አመላክተዋል (ብራውን 2000፤ ኤሊስ 1994)፡፡ በሌላ በኩል ኖሪስሆልት (2001) እና ብራውን (2000) የጠቀሷቸው ሉክማኒ (1972) ጥቅማዊ ዓላማ ያላቸው በህንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የማራቲ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች እንግሊዝኛ ቋንቋ የመናገር ብቃታቸው መጎልበቱን አመላክተዋል፡፡ ብራውን (2000) እንደሚያስረዱት በጥቅሉ ሲታይ ህንድ ውስጥ ከጥቅማዊ ዓላማ ውጭ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ውጤታማ መሆን የተለመደ አይደለም፡፡

በኤሊስ (1994) የተጠቀሱት መችኒክና ወልፍ (1982) በአሜሪካ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤቶች የስፔን ተወላጅ ተማሪዎች በውህዳዊና ጥቅማዊ መለኪያ ጥያቄዎች ተጠይቀው ለሁለቱም የተነሳሽነት ዓይነቶች በጎ አመለካከት አሳይተዋል፡፡ ሌላው ኤሊስ (1994) የጠቀሷቸው ኢልይ (1986b) በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዓመት የስፔን ተወላጅ ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ምርምር ተማሪዎቹ ለውህዳዊና ለጥቅማዊ ተነሳሽነቶች በጎ እይታ እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ ኤሊስም (1997) ተማሪዎች በአንድ ጊዜ ውህዳዊና ጥቅማዊ ተነሳሽነቶች ሊታይባቸው እንደሚችል

አመላክተዋል፡፡ ኦክስፎርድ (1996) እንደሚያስረዱት የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች (ቋንቋው ከመማሪያ ክፍላቸው ውጭ በዕለትተለት መግባቢያ መሳሪያነት ስለሚያገለግል) ከተናጋሪዎቹ ጋር የመገናኘት ዕድል አላቸው፡፡ ለምሳሌ በካናዳ እንግሊዝኛ ወይም ፈረንሳይኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ከመማሪያ ክፍል ውጭ በሚገኙበት ሁኔታ ስለሚማሩ የዚህ ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ በአንፃሩ የውጭ ቋንቋ የሚያጠኑ ተማሪዎች በአብዛኛው ጥቅማዊ ተነሳሽነትን ወይም ዓላማን ታሳቢ በማድረግ ቋንቋውን ይማራሉ (ኦክስፎርድ 1996)፡፡ በተጨማሪም ክሩክስና ስቺሚዲትን (1991)፣ ሀርዊትሰንን (1990)፣ ዶርኔይን (1990a’ 1990b)፣ ኤዩን (1988) እና ኦለርን (1981) በማጣቀስ የውጭ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን ለመማር የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጥቅማዊ ሲሆን የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ግን ውህዳዊ ለሆኑ ዓላማዎች የሚማሩ መሆናቸውን ኦክስፎርድ (1996) ያስረዳሉ፡፡

እንዳገራችንም ተነሳሽነትን በሚመለከት ተዛማጅነት (ተቀራራቢነት)አላቸው ተብለው ከተመረጡት ቀደምት ጥናቶች እንደሚከተለው ታይተዋል፡

የመጀመሪያው ተዛማጅ ጹሑፍ የስመኝ (2002) ‹‹በሁሩሙ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያላቸው ተነሳሽነት›› በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት ውጤት ነው፡፡ ስመኝ ለጥናቱ ማከናወኛ የመረጣቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅ’ የቃል መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ የተሰበሰቡትም መረጃዎች ዓይነታዊ የመተንተኛ ዘዴን ተጠቅሞ ሲሆን በጥናቱ ውጤት የተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑንና ዝቅተኛ ለመሆኑ ምክንያቱ የመማሪያ መጻሕፍትን በሚመለከት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ያላገናዘበ እንደሆነ በተጨማሪም በተማሪዎች ተነሳሽነት ዙሪያ የመምህራን ተሳትፎ የቀዘቀዘ መሆኑን በመግለጽና ለወደፊት በትምህርቱ ሂደት በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ በማሳሰብ ጥናቱን አጠናቋል፡፡

የስመኝ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነትም ልዩነትም አለው፡፡ ልዩነቱ የእርሱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀማቸው መሳሪያዎች ምልከታ ፣ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለ መጠይቅ ሲሆን ይኸኛው ጥናት የጽሑፍ መጠይቅና ፈተናን ብቻ በመረጃ መሰብሰቢያነት ተጠቅሟል፡፡ ሌላው ልዩነት የዓላማ ልዩነት ነው፤ የእርሱ ጥናት ዓላማ በተማሪዎች ተነሳሽነት ላይ ትንተና ማቅረብ ሲሆን የዚህኛው ጥናት ዓላማ ግን ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለውን ዝምድና መፈተሽ ነው፡፡ጥናቶቹ በዘመንም ይለያያሉ፡፡በሌላ መልኩ የስመኝና ይኸኛው ጥናት ሁለቱም ስለተነሳሽነት ይዘዉ ቢነሱም ይሄኛዉ ጥናት ተነሳሽነት ከዉጤት ጋር ያለዉን ዝምድና መፈተሸ ስለሆነ ተመሳሳይ አይደሉም፡፡

ሁለተኛው ተዛማጅ ጽሑፍ ዘሪቱ (2003) በአርባ ምንጭ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት የውጤት ተዛምዶ በሚል ርዕስ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናትና ምርምር ውጤት ነው፡፡ ጥናቱን ከግብ ለማድረስ የጽሑፍ መጠይቅና ፈተናን በመጠቀም መረጃዎችን ሰብስባለች፤ የተሰበሰቡትንም መረጃዎች ገላጭ መጠናዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም ተንትና በተደረገው ጥናት አማካኝነት የተማሪዎቹን የመማር ተነሳሽነት ከውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጻለች፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎቹ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት ቢኖራቸውም የፈተና ውጤታቸው ግን ከተነሳሽነታቸው ጋር መመጣጠን አለመቻሉ ነው፡፡

ለተማሪዎች የተነሳሽነትና ውጤት ተዛምዶ ልዩነት መፈጠር እንደ ምክንያት ያስቀመጠችው ለተማሪዎቹ የሚቀርብላቸው ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ጾታን' የክፍል ደረጃንና ጥቅማ ጥቅማዊ ተነሳሽነትን መሰረት ያለማድረጉ መሆኑን ገልጻ በተጨማሪም ትምህርቱ ጥቅማ ጥቅማዊ የመማር ተነሳሽነትን በሚያበረታታ መልኩ የሚቀርብ ቢሆን ተማሪዎቹ የበለጠ ውጤታማ እንደሚሆኑ በመጠቆም አስተያየትዋን ሰጥታ ጥናትዋን አጠናቃለች፡፡

ሶስተኛው ተዛማጅ ጽሑፍ ጀማል (2001)፡፡ “በሴሩ አባስ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ትንተና››በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናትና ምርምር ውጤት ነው፤ በጥናቱ ክንዋኔ የተጠቀመባቸው መረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው፡፡ የሰበሰባቸውን መረጃዎች አይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ተጠቅሞ የተነተነ ሲሆን በጥናቱ ሂደት የተማሪዎች ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑና ለዝቅተኛነቱ ምክንያት ናቸው ያላቸውን የመማሪያ መጻሕፍት በተመለከተ የተማሪዎችን የቀደመ እውቀት አለማገናዘቡን ፤ በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ የሚያደርጉት ጥረት ውስን እንደሆነ ገልፆ በትምህርቱ ሂደት ለተማሪዎች መነሳሳት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ በማሳሰብ ጥናቱን ደምድሟል፡፡

የጀማል ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚለያይበት ነገር አለው፡፡ ይኸውም እርሱ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመባቸው መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅና ምልከታ መሆናቸው አንደኛው ልዩነት ሲሆን ሁለተኛው ልዩነት ደግሞ የዓላማ ልዩነት ነው፡፡ የእርሱ ጥናት ዓላማ በተማሪዎቹ ተነሳሽነት ላይ ትንተና ማድረግ መሆኑና ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ዘመን በሴሩ አባስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 2001 ዓ.ም መሆኑ ሌላው ልዩነት ነው፡፡

ጥናቱ ከዚህኛው ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት ነገር አለው፤ ይኸውም በተማሪዎች ለሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ) ትምህርት መነሳሳት ዙርያ በመሆኑ ይመሳሰላል፡፡ሌላው ከተማሪዎች የሚሰበሰበውን መረጃ በጹሑፍ መጠይቅ ለመሰብሰብ መሞከሩ ነው፡፡

አራተኛው ለዳሰሳ የተመረጠው ጥናት በተስፋዬ ኦላና “በኢሉአባቦር ዞን በሁሩሙና በሶንጣ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸዉ ተነሳሽነትና የዉጤት ተዛምዶ” በሚል ርዕስ በ2014 በጅማ ዩኒቨርሲቲ ለመጀመርያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናትና ምርምር ነው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመባቸው መረጃ መሰብሰቢያ መሳርያዎች የጹሑፍ መጠይቅና ፈተና ናቸው፡፡ የሰበሰበውን መረጃም መሰረት በማድረግ በተማሪዎቹ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር ተነሳሽነትና በቋንቋው ትምህርት ውጤት መካካል የጎላ

ተዛምዶ አለመታየቱን፤ በተነሳሽነት አይነቶችና በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት መካከልም ተዛምዶ አለመታየቱንም አብራርቱዋል፡፡ ይሁን እንጂ በሁለተኛ ቋንቋ (አማርኛ) የመማር ተነሳሽነት በፆታ መካከል እነዲሁም የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት በትህምርት ቤትና በትምህርት ቤት መካከልም የውጤት ልዩነት ማሳየቱን ገልጹዋል፡፡ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ሁለተኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን ትምህርቱን ሲያቀርቡ የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ ቢያቀርቡ፣ ሴቶችም ሆነ ወንዶች ተማሪዎች ምን አይነት ማበረታቻ ቢደረግላቸው ውጤታማ እንደሚሆኑ አስቀድሞ በማወቅ የተማሪዎችን የመማር ተነሳሽነት ለማጠናከር የሚረዱ ተግባራትን ቢያከናውኑና ይህንኑ መሠረት ያደረገ ድጋፍና ክትትል ቢያደርጉ የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት (አማርኛ ቋንቋ ትምህርት) ተነሳሽነት ሊሻሻል ይችላል የሚሉ የመፍትሔ ሀሳቦችን በመጠቆም ጥናቱን አጠናቁዋል፡፡

ተስፋዬ ኦላና ባካሄደው ጥናትና በዚህኛው ጥናት መካከል ተመሳሳይነትም ልዩነትም አለ፡፡ ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመባቸው መሳሪያዎች ማለትም የጽሁፍ መጠይቅና ፈተና ሲሆኑ ይህም ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበት ሲሆን ይህ ጥናት ጾታንና የክፍል ደረጃን ያለማካተቱ እንደ ልዩነት ታይቱዋል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት ከተቃኙት አራት ተዛማጅ ጥናቶች ስመኝና ጀማል ጥናታቸውን ያካሄዱት በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ሲሆን የዘሪቱ ጥናት ግን በዘጠነኛና በአሰረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ እንዲሁም የተስፋዬ ኦላኒ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው፡፡

ስለዚህ አጥኚዋ ኢ-አፈፊት ተማሪዎች አማርኛን የመማር ተነሳሽነትን በተመለከተ በምትሰራበት ወረዳ የተካሄደ ጥናት ስላላጋጠማት ይህንን ክፍተት ለመሙላት ጥናቱ አስፈልጓል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱ ንድፍና አካሄድ

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

ይህ በአይነቱ መጠናዊ የሆነዉ ጥናት ገላጭ ተዛምዶአዊ የምርምር ዘዴን ተከትሎ የተካሄደ ነው።ይህ የምርምር ዓይነት የአንድን ሁኔታ ትክክለኛ ገጽታ ለማወቅ ወይም በትክክል ለመግለጽ ሲባል መረጃዎችን ከመጽሐፍት፣ ከመጠይቅና ከሌሎችም ጥናታዊ የጽሑፍ ምንጮች በማሰባሰብና የምልከታ መረጃዎችን በማጠናቀር ትንተና ለመስጠት የሚያስችል ዘዴ ነው። ገላጭ ተዛምዶአዊ የምርምር ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት ተማሪዎቹ ለሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ያለቸዉ የመነሳሳት ሁኔታና ተነሳሽነታቸዉ ደግሞ ከትምህርት ዉጤታቸዉ ጋር የሚኖረዉን ዝምድና ለመለየት ተስማሚ በመሆኑ ነዉ።

### 3.2 የናሙና አመራረጥ

#### 3.2.1 የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ለዚህ የተመረጠው የጥናት አካባቢ በጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ ቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው፡፡ በት/ቤቱ የሚማሩ አብዛኞቹ ተማሪዎች በ አፋን ኦሮሞ አፋቸውን የፈቱ መሆናቸው በቅድመጥናት ቅኝት ስለተረጋገጠ እንዲሁም ይህ ቦታ የአጥኚዋ የሥራ ቦታ በመሆኑ ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ አባላት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ማግኘትይቻላታል፣ በሚል ታሳቢም ጭምር ትምህርት ቤቱ በአላማተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጧል፡፡

#### 3.2.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ለጥናቱ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የተመረጡበት ምክንያትም ከአንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ይልቅ በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና ከዚያ በላይ በሆኑ

ደረጃዎች የሚማሩ ተማሪዎች መረጃዎችን በተሻለ ሁኔታ መስጠት ይችላሉ፤ በሚል ታሳቢ ነው፡፡ከነዚህም ውስጥ አስረኛ ክፍል በአመቺ የናሙና ዘዴ ተመርጧል፡፡

### 3.2.3 የተማሪዎች አመራረጥ

በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሁለት የ10ኛ ክፍል መማሪያ ክፍሎች ስለመኖራቸው በቅድመጥናት ቅኝት ተረጋግጧል፡፡ በዚህም መነሻነት በትምህርት ቤቱ ከ10ኛ ክፍል ተማሪዎች መካከል በኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት(የአማርኛ ቐንቐ ኢ-አፊፊት) የሆኑት በሙሉ ተለይተው ተመዝግበዋል፡፡ በዚህም አጥኚዋ በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛት ተቀራራቢ ሆኖ ስላልተገኘ ጠቅላይ ንሞና ዘዴን በመጠቀም ሁሉም የ10ኛ መማሪያ ክፍሎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጉዋል፡፡

## 3.3 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በጥናቱ ዋና ዓላማ መሠረት የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተነሳሽነትን መጠንና ዓይነት የሚያሳይ የጽሑፍ መጠይቅና የተሳታፊዎችን የትምህርት ውጤት ሊያስገኝ የሚችል የአማርኛ ቋንቋ የችሎታ መለኪያ ፈተና ናቸው፡፡

### 3.3.1 የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ የተማሪዎችን አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የመማር የተነሳሽነት መጠንን በተመለከተ መረጃ ለማግኘት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

በመጠይቁ የጥያቄዎቹ ብዛት 30 ሲሆን ሁሉም የተሳታፊዎችን አማርኛን የመማር ተነሳሽነት መጠንና ዓይነትን እንዲሁም ከውጤታቸው ጋር ያለውን ተዛምዶ እንዲለዩ ሆነው ተዘጋጅተዋል፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል 8 ውህዳዊ፣ ሰባቱ ጥቅማጥቅማዊ 7ቱ ውጫዊና 8 ውስጣዊ የተነሳሽነት ዓይነቶችን የሚለኩ ሲሆን ሁሉም ጥያቄዎች በስብጥር ቀርበዋል፡፡

በእያንዳዱ ጥያቄ ፊት ለፊት ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በጣም እስማማለሁ(5)፣ እስማማለሁ(4)፣ በመጠኑ እስማማለሁ(3) ፣ አልስማማም (2)፣ እና በጣም

አልስማማም(1) አማራጮች በሰንጠረዥ ቀርበዋል፡፡ የተገኘው ምላሽም የተለያዩ እስታቲስቲካዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ትንታኔ ተሰቶበታል፡፡

### 3.3.2 የችሎታ መለኪያ ፈተና

ፈተና የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ችሎታ ለማወቅ በመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግሏል፡፡ ፈተናው ከመዘጋጀቱ በፊት በክፍል ደረጃው መማሪያ መጽሐፍ ላይ ካሉት ይዘቶች ተማሪዎቹ የተማሯቸውን የ10ኛ ክፍል መምህራን እቅዶች፣ ከመማሪያ መጽሐፍና ከተማሪዎች የአማርኛ ደብተሮች ይለያል፡፡ ከዚያም መማሪያ መጽሐፎቹን መሠረት በማድረግና በትምህርት ቤቱ የተለመዱ የፈተና ዓይነቶችን ከግምት በማስገባት ፈተናው በጥናቱ ባለቤት ይዘጋጃል፡፡ በመቀጠልም ጥያቄዎቹ ተማሪዎቹ የተማሯቸውን ይዘቶች መሠረት ያደረጉና ክፍል ውስጥ በተለማመዱበት ሁኔታ የተዘጋጁ መሆናቸውን ለማረጋገጥም በሌሎች መምህራን ተገምግሙዋል፡፡ በመጨረሻም የሙከራ ጥናት በማካሄድ የተዘጋጀው ፈተና በዕኩል ክፋይ ዘዴ ስሌት በማካሄድ አስተማማኝነቱን በመገምገም ፈተናው ዋናውን መረጃ ለመሰብሰብ በስራ ላይ ውልዋል፡፡ የፈተናው ውጤትም በጥናቱ ባለቤት ከ100% ታርሟል፡፡

## 3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ከተጠኚዎች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ተጠይቃዊ በሆነ መንገድ በትክክል መሞላታቸው ከተጣራ በኋላ ለትንታኔ እንዲያመች ኮድ ይደረጋል፡፡ ከዚያም በውጤት መመዝገቢያ ሠንጠረዥ (ኮድ ሽት) በኮምፒውተር ላይ ይሰፍራል፡፡ ከዛም ወደ ትንታኔ ይገባል፡፡

የጥናቱን ተሳታፊ ተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ለማወቅ በተቀመጡት የመነሻ ጥያቄዎች መሠረት በመጠይቅ የሚሰበሰቡ መረጃዎችን (በSPSS version 24) ገላጭ ስታስቲክስን ማለትም የተማሪዎችን አማካይ ውጤት፣ መደበኛ ልይይትና በመቶኛ ደረጃ ምን እንደሚመስሉ ለማብራራት ተግባር ላይ ይውላል፡፡

ተዛምዶን (Correlation) አስመልክቶ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል ዝምድና መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የፒርሰን ፕሮዳክት ሞመንት(person product moment correlation) የተዛምዶ መወሰኛ ስራ ላይ ውሉአል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ትንተናና የውጤት ማብራሪያ

ጥናቱ አላማ አድርጎ የተነሳው የተማሪዎች የትምርትተነሳሽነት ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ፤ ተማሪዎች በትምርታቸው ያላቸው ተነሳሽነት ከትምርት ውጤታቸው ጋር ያለውን ጉልህ ተዛምዶ መመርመር እና የትኛው የተነሳሽነት አይነት በጉልህ ደረጃ የተማሪዎችን ውጤት ለመተንበይ ያሰችላል? የሚሉትን ለመመለስ ነው፡፡ለዚህም በመጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች መረጃ ተሰብስቡዋል፡፡በዚህ ላይ የተመሰረቱት የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## 4.1 የመረጃ ትንተና

በዚህ ጥናት በጽሑፍ መጠይቅና በፈተና የተሰበሰቡት መረጃዎች ከጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አንፃር ተተንትነዋል። የጽሁፍ ፈተናው በአምስት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን አስር እውነት ወይም ሀሰት ጥያቄዎች ፣ ምርጫ አስራ አምስት ጥያቄዎች ፣ አዛምድ አምስት ጥያቄዎች ፣ አምስት ባዶ ቦታ ሙላ ጥያቄዎች ፣ እንዲሁም ሶስት የግለጽ ጥያቄዎች በድምሩ 38 ጥያቄዎችን ያካተተ ነው። የሁሉም ተማሪዎች የፈተና ውጤትም ከመቶ የታረመ ሲሆን አማካኝ ውጤቱና የተሳታፊዎቹ አሀዝ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

*ሠንጠረዥ 1፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች አጠቃላይ መረጃና የፈተና ውጤት*

| ጾታ | ብዛጽ | ውጤታ | መ.ል (S.D) |
|---|---|---|---|
| ወ | 45 | 54.8 | 6.7 |
| ሴ | 41 | | |
| ድ | 86 | | |

ከሠንጠረዥ 1 እንደምናየው ለ86 የጥናቱ ተሳታፊዎች ለቀረበላቸው የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ከመቶ አማካይ ውጤታቸው 54.8 መሆኑን ነው፡፡ ሌላው የውጤቱ መደበኛ ልይነት (S.D) (6.7) መሆኑ በተማሪዎቹ መካከል በውጤት ረገድ በጣም የጎላ ልዩነት ያለመኖሩን ነው፡፡

የመጀመሪያው የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ት/ት የመማር ተነሳሽነት ምን ይመስላል? የሚል ሲሆን ጥያቄውን ለመመለስ የተሰበሰባው መረጃ በሰንጠረዥ-2 ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2 ተማሪዎች ለት/ት ያላቸው ተነሳሽነት አጠቃላይ ደረጃ

| ተነሳሽነት | አማካይ | መደበኛ ልይይት | ልይይት |
|---|---|---|---|
| ውጫዊ | 3.74 | 0.88 | 0.78 |
| ውስጣዊ | 3.6 | 0.72 | 0.52 |
| ጥቅማዊ | 3.8 | 0.71 | 0.505 |
| ውህዳዊ | 3.8 | 1.06 | 1.12 |

ከላይ በሰንጠረዥ-2 (ተጠኚዎቹ) አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት አይነቶች አማካይ ውጤት እና መደበኛ ልይይት ቀርቧል፡፡

በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛን የመማር ውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.74 እና መደበኛ ልይይት 0.88 ሲሆን ውስጣዊ ተነሳሽነት ደግሞ አማካይ ውጤት 3.6 ሲሆን መደበኛ ልይይቱ ደግሞ 0.72 መሆኑን ከሠንጠረዥ 2 እንረዳለን፡፡ በተጨማሪም ከዚህ ሰንጠረዥ የጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት በአማካይ ውጤት 3.8 እና መደበኛ ልይይት 0.71 እንዲሁም ውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.8 እና መደበኛ ልይይት 1.06 መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በሰንጠረዥ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየን የተማሪዎቹ አማርኛን የመማር ተነሳሽነት አይነቶች መካከል ጥቅማጥቅማዊና ውህዳዊ የተነሳሽነት አይነቶች የተሻለ ውጤት (3.8)

ያሳዩ ሲሆን ከእነዚህ በመቀጠልም ውጫዊ ተነሳሽነት በሦስተኛነት ሲጠቀስ (3.74) ውስጣዊ ተነሳሽነት በ3.6 የመጨረሻውን ደረጃ ይይዛል፡፡

ይህም የሚያስረዳን የቢፍቱ ጊቤ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች አፋቸውን በአፋን ኦሮሞ የፈቱ አማርኛን ቋንቋ ትምህርትን የሚማሩት በዋናነት በውህዳዊና ጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት ደረጃ መሆኑ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎቹ በውስጣዊ መነሳሳት ደረጃ አማርኛን የመማራቸው ሁኔታ ከሌሎቹ አንጻር ዝቅተኛ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ መሪ ጥያቄ “ የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?” የሚል ነው፡፡ ይህንን የውጤትና የተነሳሽነት ግንኙነት ለመፈተሽ ከላይ በሰንጠረዥ 1 እና 2 የቀረበውን የፈተና ውጤትና የተነሳሽነት ሁኔታ እንደ ግብአት በመጠቀም በ SPSS ሶፍትዌር አማካኝነት የተዛምዶ መጠን በሰንጠረዝ ሶስት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

*ሰንጠረዥ 3፡ የተነሳሽነት አቅጣጫዎች እና የአማርኛ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ*

| ተለዋዋጭ | ውስጣዊ | ውጫዊ | ጥቅማጥቅማዊ | ውህዳዊ | ውጤት |
|---|---|---|---|---|---|
| ውስጣዊ | 1.00 | - | - | - | - |
| ውጫዊ | 0.216<br>P = 0.32 | 1.00 | - | - | - |
| ጥቅማጥቅማዊ | - 0.397<br>P = 0.28 | 0.22<br>P = 0.4 | 1.00 | - | - |
| ውህዳዊ | 0.24<br>P = 0.28 | - 0.288<br>P = 0.45 | - 0.299<br>P = 0.5 | 1.00 | - |
| ውጤት | 0.00636<br>$P=5.9X10^{-8}$ | - 0.28<br>$P=2.4 X10^{-7}$ | 0.3258<br>$P=1.4 X10^{-7}$ | 0.398<br>$P=4 X10^{-8}$ | 1.00 |

*የናሙና ብዛት 86* $*P<0.05$ $**P>0.05$

በተነሳሽነት አይነቶቹና በአማርኛ ትምህርት ውጤት መካከል የጎላ ተዛምዶ መኖሩን ሰንጠረዥ 3 ያሳያል፡፡ በውህዳዊ ተነሳሽነትና በውጤት መካከል ያለውን ተዛምዶ ስንመለከት የ 'P' ዋጋ 4x10$^{-8}$ ነው፡፡ ይህም ከ 0.05 በታች በመሆኑ ተዛምዶ መኖሩን ያሳየናል፡፡ የተዛምዶውን መጠን ለመወሰን የ 'r' ዋጋን መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በተነሳሽነት እና በትምህርት ውጤት መካከል ዝምድና መኖሩ የሚረጋገጠው የ 'r' ዋጋ በ -1 እና በ 1 መካከል ሲመጣ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በውህዳዊ ተነሳሽነትና በውጤት መካከሌ ጎሌህ አወንታዊ ተዛምዶ (r=0.398, P<0.005) መኖሩን ሰንጠረዡ ያመለክታል፡፡ ይህም ነጻ ተለዋዋጩ ውህዳዊ ተነሳሽነትና ጥገኛ ተለዋዋጩ ውጤት 15.84% ባህሪ የሚጋሩ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአማርኛ ውጤትና በጥቅማጥቅማዊ ተነሳሽነት መካከል ያለው ዝምድና ከሰንጠረዡ ስንመለከት (r=0.3258, P<0.05) ጉልህ አወንታዊ ተዛምዶ መኖሩን እና 10.6% ባህሪ መጋራታቸውን እንመለከታለን፡፡ ይሁን እንጂ በአማርኛ ውጤትና በውስጣዊ ተነሳሽነት መካከል ዝምድና የለሽ ወይም በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ መኖሩን (r=0.00636,P<0.05) እና 0.004% የጋራ ባህሪይ ብቻ መጋራታቸውን ከሰንጠረዡ እንመለከታለን፡፡ በሌላ በኩል በአማርኛ ውጤትና በውጫዊ ተነሳሽነት መካከል ያለው የተዛዶ መጠን ጉልህ ቢሆንም አሉታዊ መሆኑን (r=-0.28, P<0.05) እንዲሁም 7.84% ባህርይ የሚጋሩ መሆኑን ከሰንጠረዥ 3 እንረዳለን፡፡

ሌላው ሰንጠረዥ 3 የሚያሳየው የተነሳሽነት አይነቶች መካከል እርስ በርስ ያላቸው ተዛምዶ ነው፡፡ ይህንንም ስንመለከት በሁሉም መካከል ያለው የ 'ፒ' ዋጋ ከ0.05 በላይ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሚያስረዳው አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነት አይነቶች መካከል ምንም ዝምድና ያለመኖሩን ነው፡፡

## 4.2. የውጤት ማብራሪያ

የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል ኢ-አፋፊት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ት/ት የመማር ተነሳሽነታቸው ከውጤታቸው ጋር ያለው ዝምድናን የሚያመለክት ሲሆን 86 ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ በ30 ጥያቄዎች የተደረጃ የጽሑፍ መጠይቅና እንዲሁም 38 ጥያቄዎችን ያካተተ ፈተና ለመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባራዊ ሆንዋል፡፡ የተሰበሰበውን መረጃ መሠረት

በማድረግም የተማሪዎቹ አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ከውጤት ጋር ያለው ተዛምዶ፤ ከተነሳሽነት ዓይነቶች ይበልጥ ከውጤት ጋር ዝምድና ያለው የቱ እንደሆነና የተነሳሽነት አይነቶች እርስ በርዕስ ያላቸው ዝምድና ምን እንደሚመስል ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

ከጥናቱ መሪ ጥያቄዎች የመጀመሪያው ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን የመማር ተነሳሽነታቸው ምን እንደሚመስል ለማረጋገጥ የቀረበው ጥያቄ ነው፡፡

ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በሠንጠረዥ 3 ላይ የተቀመጠውን ትንታኔ ስንመለከት የተማሪዎቹ አማርኛ የመማር ተነሳሽነት አማካይ ውጤት ከትልቁ ወደ ትንሹ በቅደም ተከተል ጥቅማዊ ተነሳሽነት እና ውህዳዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት እኩል 3.8፣ ውጫዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.74፣ እንዲሁም የመጨረሻው ውስጣዊ ተነሳሽነት አማካይ ውጤት 3.6 መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በመነሳት የተማሪዎቹ አማርኛን የመማር ተነሳሽነት ጥሩ የሚባል ደረጃ መሆኑን ማወቅ ተችሏል፡፡ ነገር ግን በሰንጠረዥ 1 ከተሰጠው የተማሪዎች የፈተና አማካይ ውጤትን ስንመለከት (54.8%) ከዝቅተኛ የማለፊያ ውጤት ብዙም ያልራቀ ነው፡፡

አማካይ የተነሳሽነት ደረጃቸውን ስንመለከት ግን 3.735 ነው፡፡ ይህም ወደ መቶኛ ሲቀየር 74.7% ነው፡፡ ይህም ማለት ውጤታቸውና የተነሳሽነት ደረጃቸው ያለመጣጣም አዝማሚያ ነው ያለው፡፡

የተማሪዎቹ ተነሳሽነትና የፈተና ውጤታቸው አለመጣጣም ምክንያት የትምህርቱ አቀራረብ ወይም የመማር ማስተማር ሂደቱ ከተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት ሊያሰጥ ይችላል፡፡ ይህም በክፍሌ (2002) የተጠቀሱት Devis (1999) የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ራሳቸውን የቻሉ እንዲሆኑና በዚህም በትምህርቱ ውጤታማ እንዲሆኑ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ተከታታይነት ያለው ወቅታዊ የሆነ የተማሪዎችን እምነት አጠናክሮ በደንብ እንዲሰሩ የሚያሰችል አዋንታዊ ምላሽ መስጠት እንደሚጠበቅባቸው እንዲሁም በጣም ቀላል በጣምም ከባድ ያልሆኑ ተግባራትን በመስጠት ተማሪዎች ስኬታማ የሚሆኑበቸውን

አጋጣሚዎች ማመቻቸት ከሚቀርቡላቸው የትምህርት መሳሪያዎች ውስጥ የራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ የሚያንፀባርቁ ትርጉሞችን እንዲፈልጉ ማድረግ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ ፣ዋጋ ያላቸው ጠቃሚ የትምህርት ማህበረሰብ አባላት መሆናቸው እንዲሰማቸው ሞራላቸውን መጠበቅና ውስጣዊ ተነሳሽነታቸውን ከፍ ማድረግ እንዳለባቸው ከገለጹት ሃሳብ ጋር የሚስማማ ይመስላል፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ Ellis (1995) የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት ከፍተኛ ሆኖ የትምህርት ውጤት ዝቅተኛ መሆን ዝቅተኛ ተነሳሽነት ዝቅተኛ ውጤትን፣ ዝቅተኛ ውጤት ደግሞ መልሶ ከፍተኛ ተነሳሽነት እንደሚያስከትል በሚል ከደረሱበት ድምዳሜ ጋር ይቃረናል፡፡ እንደ ኤሊስ ድምዳሜ ቢሆን ኖሮ በዚህ ጥናት ሂደት ውስጥ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ከፍተኛ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና አነስተኛ ውጤት ማስመዝገብ አልነበረባቸውም ነበር፡፡

የጥናቱ ሁለተኛ መሪ ጥያቄ ስንመለከት የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ት/ት ውጤታው ጋር ያለውን ተዛምዶ በተመለከተ ነው፡፡ በሰንጠረዥ 3 እንደተመለከተው በተደረገው ትንተና ከተነሳሽነት አይነቶች መካከል ጥቅማጥቅማዊ እና ውህዳዊ የተነሳሽነት አይነቶች ከፍተኛ ውጤት ጋር ጉልህ አወንታዊ ተዛምዶ ታይቷል፡፡ እንዲሁም በውጤትና በውጫዊ ተነሳሽነት መካከል አሉታዊ ቢሆንም ጉልህ ተዛምዶ የታየ ቢሆንም በውጤትና ውስጣዊ ተነሳሽነት መካከል በጣም ዝቅተኛ ተዛምዶ ታይቷል፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ በውጤትና በተነሳሽነት መካከል ተዛምዶ መኖሩን ሰንጠረዥ 3 ያመለክታል፡፡ ይህም ውጤት ከበርካታ ተመራማሪዎች ለምሳሌ በብራውን (2000፣1994) ዋቢነት ከጋርድሃርኒ ላምበርት (1959፣1922)፣ ከብሬውን (2000) እና ኖረስ ሆልት (2001) ከጠቀሷቸው ከሉክማኒ (1972) እና ከሀርመር (2001) የምርምር ውጤቶች ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያ፣ መደምደሚያና መፍትሄ

የጥናቱ ዳራ፣ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ክለሳ ድርሳናት፣ የአጠናን ዘዴና የጥናቱ ውጤት ትንተና ማብራሪያ እንደ ቅደም ተከተላቸው ያለፉት ምዕራፎች ትኩረት ነበሩ፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ማጠቃለያና መደምደሚያ እንዲሁም ሃሳቦች በቅደም ተከተል ይቀርባሉ፡፡

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የ10ኛ ክፍል የአፋን ኦሮሞ አፍ-ፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነትና ውጤት ተዛምዶ መመርመር መሆኑ በቀዳሚ ክፍሎች ለማሳየት ተሞክሯል፡፡
በዚህም መሠረት ጥናቱ ምላሽ ሊሰጥባቸው መሪ አድርጎ ያነሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች የሚከተሉት ነበሩ፡-

- በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር ተነሳሽነት ምን ያህል ነው?
- የተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነት ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤታቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል?

በዚህም መሠረት በመጀመሪያ ተጠኚዎችና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ተመርጠዋል፣ ተዘጋጅተዋል፡፡ ተጠኚዎቹ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን ቀርሳ ወረዳ በቢፍቱ ጊቤ ሁለተኛ ትምህርት ቤት 10ኛ ክፍል የሚማሩ 86 ተማሪዎች ናቸው፡፡
የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጽሑፍ መጠይቅና የፈተና ውጤት ነው፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎችም የተለያዩ ስታቲስቲካዊ ማሳያ ዘዴዎች ተግባራዊ በማድረግ የጥናቱ ውጤት ተተንትኗል፡፡

በውጤቱም የተማሪዎቹ የመማር ተነሳሽነት ከፈተና ውጤት ጋር ተዛምዶ ያለው ቢሆንም ውጤታቸው የተነሳሽነታቸውን ያክል ያለመሆኑ ሂደቱ ዙሪያ ትልቅ ስራ መስራት እንደሚያስፈልግ ይህ ካልሆነ ግን የተማሪዎችን የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ውጤት በቀጣይነት ሊጎዳ እንደሚችል ከጥናቱ ውጤት መገመት እንደሚችል የአጥኚዋ እምነት ነው፡፡

## 5.2. መደምደሚያ

ከፍ ሲል በተናጥል የተጠቀሱትን የጥናቱን ውጤቶች መሠረት ማድረግ ጥናቱ ከሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ደርሷል፡፡

- ተማሪዎች ተነሳሽነት እንዳላቸውና ደረጃውም ከፍ ያለ እንደሆነ ታይቷል፡፡
- ተማሪዎች ያላቸው ተነሳሽነትና የትምህርት ውጤታቸው በስታቲስቲክስ ጉልህ ተዛምዶ ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በተጨማሪም የተነሳሽነት አይነቶች እርስ በርሳቸው ዝምድና እንደሌላቸው ታይቷል፡፡

## 5.3. የመፍትሄ ሀሳብ

አጥኚዋ በጥናቱ ትንታኔ ላይ በመመርኮዝ ማብራሪያና መደምደሚያን ተከትሎ የሚከተሉትን አስተያየቶች በመፍትሔ ሀሳብነት አቅርባለች፡፡

- በክፍል ውስጥ የቋንቋ መምህራን የተማሪዎች የመማር ተነሳሽነት መኖር ወይም አለመኖር በትምህርት ውጤታቸው ላይ የበኩሉን ተጽእኖ እንደሚያሳድር በመገንዘብ፣ የቋንቋ ትምህርቱን የተማሪዎችን ፍላጎትና ስሜት በሚያነሳሳ መልኩ ቢያቀርቡ፤
- መምህራን ከትምህርት አቀራረባቸውም በተጨማሪ የተማሪውን ተነሳሽነት ወደ ውጤት ሊቀይሩ የሚችሉ ስልቶችን በመጠቀም የተማሪዎች የውጤት መሻሻል ላይ ቢሰሩ፤

- የሰርዓተ ትምህርት ቀራጮችና የትምህርት መሳሪያ አዘጋጆች በዝግጅታቸው ወቅት የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎችን የተነሳሽነት ሁኔታ ከግምት ቢያስገቡ፤
- በአጠቃላይ ኢ-አፈፈት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ የመማር ተነሳሽነታቸው የጎላ ሊሆን የሚችል ቢሆንም  በውጤት ረገድ ዝቅተኛ ሊሆኑ ስለሚችሉ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

# ዋቢ መጻህፍት


ስመኝ፡ አባሁና፡፡ (2002) ፡፡ በሁሩሙ ሁለተኛ ደረጃትምህርት ቤ/ትየ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ያለቸዉ ተነሳሽነት፡፡ለመጀመርያ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ጅማ ዩንቨርስቲ፡፡(ያልታተመ)

አለም እሼቱ፡፡(1994)፡፡ መሰረታዊ የምርምር እና የዘገባ አጻጻፍ ፡፡ አዲስ አበባ የንግድ ማተሚያ ቤት፡፡

ዘሪቱ አስፋዉ፡፡ (2003) ፡፡በጋሞኛ ቋንቋ አፋቸዉን የፈቱ ተማሪዎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት

ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ፡፡ለሁለተኛድግሪ ማሟያነት የቀረበ ፅሁፍ፡ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ፡፡

ክፍሌ ሰበረዉ፡፡ (2002)፡፡ አፋቸዉን በጉሙዝኛ ቋንቋን የፈቱ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነትና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዉጤት ተዛምዶ ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ፅሁፍ ባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡(ያልታተመ)፡፡

እባቡ‹ንጉሴ፡፡(2000)፡፡ በሰቃ 2ኛ፡፡ደረጃትምህርት/ቤት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የክፍል ዉስጥ ተሳትፎ፡፡ ጅማ ዩኒቨርሰቲ፡፡(ድ.ማ.ፅ)፡ ፡ያልታተመ፡

ጀማል ባዲ (2001) ፡፡በሴሩ አባስ 2ኛ ደረጃትምህርትቤት የ9ኛ ክፍልተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት ትንተና በጅማ ዩኒቨርሰቲ፡፡ያልታተመ፡፡

ያለዉ እንዳወቀ፡፡ (1998) የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፡፡ ባህርዳር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሰቲ፡፡

Bachman (2010). Language assessemente in practice oxford university press.

Brown.H. D, (2000), principles of language learning and teaching (2nd Ed) USA.longmanInc.

Brown H.D. (1994) principles of language learning and teaching (3rd Ed) USA. Sanfarancisco state university.

Brown.HD (1997).Princples of Language learning and teaching (2nd Ed) New Jersey, premire Hall

Chatterjee, S.k (2000) advanced Educational psycology, publisher.

Cole, G.P.andchan, k.s (1994) teaching princples and practes, Australiya, prentice Hall

Dorneeyei, Z. (2001) Teaching & Researching Motivation London education limited.

Elis.R. (1997) second language Acquisition oxford; oxford university press.

Elliot, J.G.etal (2005) motivation, Engagement and education performance.interbational

Perspective on the contexts for learning New York: pellagara.

Freeman, D.L. and Long, M.H. (1992) An introducation to second language aequisition research (3rd edit) New York Longman group UK lit.

Gardner.R.C.(2004), Attitude motivation Test battery. International AMTB Research

Project. The university of westernontario, Canada Retrieved April, 2011.

Gardner.R.C (2003) <<Attitudes, Motivation and second language learning. Ameta .Analysis

of studies.

Gardner .R.c (2001) Intergrativ motivation and second language Acuquision.in z

Gardner.R.C (1985) social psycology and second language learning.therolof attitudesand motivation. London: Arnold.

Gardener R.C.(1982) language attitude and language learning in Ryan E.B(Ed),attitudesTowards Language variation:social and applied contex.Britain Edward Arnold.

Hamner,J(1991).The practice ofenglish language Teaching.londonlogmanLittle Wood,W.(1981) communicative language Teaching.cambridge:Cambridge university. Press.

Little Wood.W (1981). Communicatiive Language Teaching Cambridge: Cambirdge Univerity Paress.

Noels, K.A.etal (2003)<<Way are you learning asecondlanguage?motvational orientation Andseetdeterminatio theory>>language learning.

Norris-Holt j. (2001). Motivation as a contributing factor in second Language acquisition. Retreved April 6, 2001, Current issue. Activitites for ESL students. Things for ESL teachers. Jacqui Japan (at) Hotmail, Japan, the internet TESOL Journal.

Pintriitch, R. and Schunk. H. (2002) Motivation in Education theory, research and applications New York: Mirill prentice hall.

Scott Kissau.(n.d)gendere differences in second language motivation, An investigation of Micro.and Macro- level infuences.Refrievedapril 5,2011.

Skinner,E.C(1959)Educational psycology($4^{th}$ Ed) newyork,prenties Hall, Inc.

Stern H.H(1994) fundamental concept of language Teaching.HongKong:oxford university press.

Stipek (1996) ,motivation and introduction in siman hand book of education USA university of California losangelus.

Ur,P.(1996) Acourse in language teaching cambridge oxford univrsty press.

Williyam, M.M, Burdan, B(1997),psycology for language teachers. Asocial constractivia approach. cambrige oxford university press.

አባሪ - ሀ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲይስ ኮሌጅ**

## የድህረምረቃ ትምህርት ቤት

## የአማርኛ ቋንቋና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል

**ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አማርኛን ለመማር ያላቸዉ ተነሳሽነት እና የዉጤት ተዛምዶ ፍተሻ በሚል ርዕስ ለሚደረግ ጥናት ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጀ የጽሁፍ መጠይቅ**

ውድ ተማሪዎች፡- ርዕሱ ከላይ ለተጠቀሰው የሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ ጥናታዊ ጽሁፍ በመረጃ ሰጪነት ትሳተፉ ዘንድ ተጋብዛችኋል፡፡ለበጎ ትብብራችሁና መልካም ተሳትፏችሁም ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

የመጠይቁ ዋና አላማ ከላይ ለተጠቀሰዉ የጥናት ርዕስ መረጃ መሰብሰብ ነዉ፡፡ በመሆኑም በሂደቱ የሚገኘዉ መረጃ ለጥናቱ እንደ ግብዓት ከማገልገሉ ባሻገር ለሌላ ተግባር የማይዉል መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ፡፡

**ክፍል አንድ፡-** ዳራዊ መረጃ፡

ጾታ፡- ☐ ወንድ ☐ ሴት

የአፍ መፍቻ ቋንቋ፡- ☐ አፋን ኦሮሞ ☐ አማርኛ ☐ ሌላ

**ክፍል ሁለት**፡- ቀጥሎ ባለዉ ሰንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡትን ዓ.ነገሮች ካነበብክ(ሽ) በኋላ ተስማሚ ሆነዉ ከፊት ለፊቱ ካሉት አማራጭ መልሶች የ √ ምልክት በማድረግ ስምምነትህን (ሽን) ግለጽ(ጪ)

የተሰጡት አማራጮች መግለጫ፡

5- በጣም እስማማለሁ 4- እስማማለሁ 3- በመጠኑ እስማማለሁ 2- አልስማማም

1- በጣም አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዐይነት | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አማርኛ ቋንቋን ስማር በጣም እደሰታለሁ | ውስ | | | | | |
| 2 | አማርኛ መማር ጠቃሚ ነዉ፡፡ምክንያቱም አማርኛን ከሚናገሩ ወገኖች ጋር በቀላሉ ለመግባባት ያስችለኛል፡፡ | ውጫ. | | | | | |
| 3 | አማርኛ ቋንቋን መማር ቢከብደኝም መማር አልጠላም | ውስ | | | | | |
| 4 | በአማርኛ ቋንቋ በሁሉም ክሂሎች ጎበዝ መሆን ምኞቴ ነው | ውስ | | | | | |
| 5 | ወላጆቼ አማርኛ እንድማር ሊረዱኝ ይሞክራሉ | ውጫ | | | | | |
| 6 | አማርኛን መማር ጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ከተለያዩ ሰዎች ጋር ለመገናኘትና ለመግባባት ይረዳኛል | ውህ | | | | | |
| 7 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያልገቡኝን ከመምህሬ ጠይቄ መረዳት እንድችል ወላጆቼ ይገፋፉኛል | ውጫ | | | | | |
| 8 | አማርኛን የምማረዉ በአማርኛ ቋንቋ የተሰሩትን ፊልሞችና ሙዚቃዎች ለመከታተልና ለመረዳት ነዉ | ውህ | | | | | |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ መናገር መቻሌ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚኖረኝን ቅቡልነት ይጨምራል | ውህ | | | | | |
| 10 | አማርኛን መማር ጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ከተለያዩ ሰዎች ጋር ለመገናኘትና ለመግባባት ይረዳኛል | ውህ | | | | | |
| 11 | አማርኛን መማር ጠቃሚ ነዉ ምክንያቱም ለወደፊት ሙያዬ ያስፈልገኛል | ጥ | | | | | |
| 12 | አማርኛን መማር ይጠቅማል ምክንያቱም የቋንቋዉን ተናጋሪዎች የኑሮ ስልት በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል | ጥ | | | | | |
| 13 | አማርኛን መማር የሚያስፈልገዉ ጥሩ ስራ ለማግኘት ስለሚጠቅም ነዉ | ጥ | | | | | |
| 14 | አማርኛን መማር ይጠቅማል ምክንያቱም አማርኛን በማወቄ ሌሎች ሰዎች ስለሚያከብሩኝ ነዉ | ውህ | | | | | |
| 15 | አማርኛን መማር የሚጠቅመዉ በሌሎች ዘንድ አዋቂ ስለሚያስብል ነው | ውጫ | | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 16 | አማርኛ መማሬ ለኔ ጠቃሚ ነው ምክንያቱም የአመለካከት አድማሴን ያሰፋዋል | ውስ | | | | | |
| 17 | አማርኛ ቋንቋን መናገር መቻሌ ማህበራዊ መስተጋብሬን ከፍ ያደርገዋል | ውህ | | | | | |
| 18 | አማርኛ ቋንቋን የምማርበት ምክንያት የተለያየ አካባቢ ስጉዋዝ እንዳልቸገር ነው | ውህ | | | | | |
| 19 | አማርኛ ቋንቋን የምማረው ፈተና ለማለፍ ነው | ጥ | | | | | |
| 20 | አማርኛን መማር ሙሉ ሰው ያደርጋል | ውስ | | | | | |
| 21 | ወላጆቼ በተቻለኝ መጠን አማርኛ እንድለማመድ ያበረታቱኛል፡፡ | ውጫ | | | | | |
| 22 | በሌሎች ቋንቋዎች ከሚተላለፉት ይልቅ በአማርኛ ቋንቋ የሚተላለፉ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን የበለጠ እከታተላለሁ | ውስ | | | | | |
| 23 | አማርኛ ከምወዳቸዉ ትምህርቶች አንዱ ነዉ፡፡ | ውስ | | | | | |
| 24 | ወላጆቼ እስከ መጨረሻ በአማርኛ ትምህርት እንድቀጥል ይመኛሉ | ውጫ | | | | | |
| 25 | በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የመረዳት ችግር ሲገጥመኝ ሁል ጊዜ የአማርኛ መምህሬን እገዛ እጠይቃለሁ | ውስ | | | | | |
| 26 | አማርኛ ቋንቋን ከአካባቢው ማህበረሰብ ባለኝ ግንኙነት ምክንያት እማራለሁ | ውጫ | | | | | |
| 27 | በክፍል ውስጥ አማርኛ ቋንቋን በደንብ የምማርበት ምክንያት ችሎታዬን ለቤተሰብ/ለጉዋደኛ ማሳየት ስለምፈልግ ነው | ውህ | | | | | |
| 28 | አማርኛን በተሻለ መንገድ ከተማርኩ የተሻለ ስራ አገኛለሁ | ጥ | | | | | |
| 29 | የአማርኛ ቋንቋ ችሎታዬን ማሻሻል ገንዘብ ለማግኘት ያስችለኛል | ጥ | | | | | |
| 30 | አማርኛ ቋንቋ መናገር ከቻልኩ ጥሩ ኑሮ እኖራለሁ | ጥ | | | | | |

አባሪ ለ :

የአማርኛ ፈተና

ለቢፍቱ ጊቤ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለ10ኛ ክፍል የተዘጋጀ የችሎታ መለኪያ ፈተና 2015ዓ.ም

**<u>ትዕዛዝ አንድ</u>፡ የቀረቡትን ጥያቄዎች እውነት የሆነውን እውነት ሀሰት የሆነውን ሀሰት በማለት መልሱ**

1. ቋንቋ አንደበታዊና ስርዓታዊ የሆነ የሰው ልጅ መግባቢያ ነው፡፡
2. የቋንቋን አመጠጥ ከአዝግሞተ ለውጥ ጋር የሚያገናኙት ቁስ አካላዊያን ናቸው፡፡
3. ሀረግ ከቃል የሰፋ ከዐ.ነገር ያነሰ መዋቅር ነው፡፡
4. ልቦለድ ከደራሲው ምናባዊ ፈጠራ ጋር የተቋራኘ ነው፡፡
5. በጥሩ ሁኔታ የተጻፈ አንቀጽ ሁሉ ኃይለ ቃል የለውም፡፡
6. አያያዥና መሸጋገሪያ ቃላት ምንም ተግባር የላቸውም፡፡
7. ከቋንቋ ባህሪያ ውስጥ አንዱ ተዋዋሽነት ነው፡፡
8. ቁጥብነት የአጭር ልቦለድ ባህሪ ነው፡፡
9. በአንድ ልቦለድ ውስጥ ታሪኩ የተፈጸመበት ዘመንና ቦታ የሚያሳየን ትልም ነው፡፡
10. የቃላት ስብስብ ሁሉ ዐ.ነገር ሊመሰርት አይችልም፡፡

**<u>ትዕዛዝ ሁለት</u>፡ ከዚህ በታች የተለየዩ ቋንቋ ነክ የምርጫ ጥያቄዎች ቀርበዋል እንደ አጠያየቃቸው ባህሪ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ**

11.ከሚከተሉት አማራጮች መካከል ያለንበት ልዩነት የተለያዩ ትርጉሞች ሊሰጥ የሚችለው የቱ ነው? ሀ. በቅሎ ለ. ብል ሐ. እንጀራ መ. ሁሉም መልስ ነው

12. ታታሪ ከሚለው ግስ የሚመሰረተው ቅጽል የቱ ነው?

ሀ. ተተለተለ ለ. ተረተረ ሐ.ታታሪ መ. መልሱ አልተሰጠም

13. አገደ ለሚለው ቃል ተቃራኒ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ተበቀ ለ. ፈቀደ ሐ. ከለከለ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

14. ሙና ከትምህርት ቤቱ ተማሪዎች መካከል አንገተ ሰባራ ወጣት ናት፡፡ ስሩ የተሰመረበት ሀረግ ትርጉም

ሀ. አይናፋር ለ. ጎበዝ ሐ. ተናጋሪ መ. አጎንብሳ የምትሄድ

15. ከሌሎች ሀረጋት ልዩ የሆነና የሀረጉ መሪ ከሀረጉ በስታ ግራ እና በስተ ቀኝ የሚገኘው የሀረግ አይነት ____________

ሀ. ስማዊ ሀረግ ለ. ግሳዊ ሀረግ ሐ. ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ መ. መልስ የለውም

16. አረምን መንቀል ስር ሳይሰድ ነው ለሚለው ምሳላዊ አነጋገር

ሀ. ችግር ሳይበረታ በቶሎ መፍትሔ ለመሻት ለ. የምቀኝነት መጥፎነትን ለመግለጥ ሐ. ስግብብነትን የሚገልጽ መ. ሁሉም መልስ

17.ሰዎች ዕድሜያቸው ከገፋ በህይወት የካበቱትን ልምድና እውቀት ጥልቅና ሰፊ መሆኑን የሚያመለክት አባባል የቱ ነው?

ሀ. አድሮ ቃሪያ ለ. ዕድሜ መስታዎት ነው ሐ. ከረጁ አይበጁ መ. ሁሉም

18. ግጥምን በጥቂት ቃላት ብዙ መግለጽ የሚችል የስነ ጽሁፍ ዘርፍ መሆኑን ለመግለጽ የሚያገለግል ባህሪው የቱ ነው?

ሀ. ቁጥብነት ለ. ምጣኔው ሐ. ቀለሙ መ. ግጥማዊ አደራደሩ

19. ከቤጤዎቿ ፈተና የነቃችው ጎበዝና ብልህ ነበረች በዚህ ዐ.ነገር ውስጥ ስሩ የተሰመረቤ ቃል ትርጉም ___________

ሀ. ከዘመድ አዝማዷ ለ. ከባልደረቦቿ ሐ. ከእኩዮቿ መ. ከአጋሮቿ

20.እንደ ታላቅ ልጅ የሚለው ሀረግ ምን አይነት ሀረግ ነው?

ሀ. ቅጽላዊ ሀረግ ለ. ስማዊ ሀረግ ሐ. ተውሳከ ግሳዊ መ. መ.አልተሰጠም

21.ማገጠ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ ሊሆን የሚችለው የቱ ነው?

ሀ. ባለገ ለ. ተበላሸ ሐ. ዋልጊ ሆነ መ. ሁሉም

22.ሞኝ የእለቱን ________ የሚለው ምሳሊያዊ አነጋገር የሚያሚል ________ነው

ሀ. ብልህ ያዓመቱን ለ. ደሀ የድግሶን ሐ. ነበዝ የወዙን መ. ሁሉም መልስ ናቸው

23. አንቺ ባንድራ ፍረጂ! የሚለው አገላላጽ የቀረበበት የዘይቤ አይነት

ሀ. ምጸት ለ. ግነት ሐ. እንቶኔ መ. ሰወኛ

24.ከሚከተሉት ቃላት መካከል ቃን ከምንጠቀምበት ነገር አንጻር ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ደነደነ ለ. ሰባ ሐ. ግዜፍ ሆነ መ. ለደለደ

25.ጤፍ ከወንድሟ ጎተራ ትሞላለች የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር የሚገልታ ____ነው?

ሀ. ስግብግብነትን ለ. ጀግንነትን ሐ. የመተባባር ጠቀሜታ መ. ንቀትን

**ትእዛዝ አራት፡ በ "ሀ" ረድፍ ለተዘረዘሩት ፈሊጣዊ አነጋገሮች ፍቺ ሊሆኑ የሚችሉ በ"ለ" ረድፍ ስር ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ**

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. የጥርስ ስጋ | ሀ. የብዙ ልጆች እናት |
| 2. ሀብቷ ቀና | ለ. ቆንጆ |
| 3. ባህር ወለድ | ሐ. ጨቅጫቃ |
| 4. ማቅ መሰለች | መ. ጥቁርቁር |

5. ደመ ግቡ　　　　　　　ሠ. ታጨች

ረ. አይናፋር

ቀ. ፀባየ መልካም

**<u>ትዕዛዝ አምስት፡</u> ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳ ቦታ ውስጥ ትክክለኛውን መልስ በመጻፍ መልሱ**

1. ሁለቱ ሰዎች ወይም ሁለት ቡድኖች ዳኞች በመሰየም የሚያደርጉት ስርዓት ያለው ሙግት ______________________________ ይባላል?
2. ስለ ግጥም ባህሪያት ትንታኔ የምንሰጥበት የእውቀት ዘርፍ ምን ይባላል?
3. በግጥም ውስጥ የቀለማትና መጠን በሀረግ ውስጥ የምንወሰንበት ______ ይባላል?
4. አንድ ነገር ምስልና ገጽታ በቃላት አማካኝነት ስሎ ለማቅረብ የሚሞክር የጽህፈት አይነት ______________________________ ይባላል?
5. በአጠገብ የሌለን ሰው ወይም ሰው ያልሆነን ነገር በቅርብ እንዳለ እንደሚሰማንና መልስ እንደሚሰጠን አድርገን የምናወራው የዜይቤ አይነት____________ ይባላል?

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች የፊደል ግድፈት ሳይኖር የእጅ ጽሑፍ ምላሻቹን ስጡ

1. አስተማማኝነቱን ለሚለው ቃል በምዕላድ በመተንተን አሳዩ
2. እንደ ገንቦ ጠላ በድንደቀደቂ
   እንደ ጎሮ ጎመን ብትንከረፈፌ
   ወደደኝ ወደድኩት ከእንግዲህ እረፊ
   ለሚለው ቃላቂ ግጥም ምንን ለመግለጽ እንደተገጠመ አብራሩ
3. የሀረግ አይነቶች ስንት እንደሆኑ በመግለጽ ዘርዝሯቸው

# የአጥኚዋ ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች ስሜ የተጠቀሰው አጥኚ ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ የግል ስራዬ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለው፡፡ በጥናቴ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን መሳሪያዎችና ስራዎች በሙሉ በዋቢ መጽሀፍት ስር በማስቀመጥ ዋጋ ሰጥቼባቸዋለሁ፡፡

የአጥኚዋ ስም -----------------

ፊርማ -------------------------